# ለጽህፈት ክሂል የተመረጡት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች እንዴት ተደራጅተዋል ?

(በአዲስ አበባ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ
ለመጀመሪያ ደረጃ የሁለተኛ እርከን (5-8)
በተዘጋጁት የአማርኛ መጻህፍት ላይ
የተደረገ የይዘት ትንተናና ግምገማ)

በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን
በማስተማር ስነዘዴ ለማስተርስ
ዲግሪ ሟሟያ የቀረበ
ጥናት


በ

ጽጌ ታፈሰ


ግንቦት 1992 ዓ.ም

# በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

**ለጽህፈት ክሂል የተመረጡት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች እንዴት ተደራጅተዋል?**

**(በአዲስ አበባ መስተዳደር ትምህርት ቢሮ ለመጀመሪያ ደረጃ**

**የሁለተኛ እርከን (5-8) በተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ**

**መፃህፍት ላይ የተደረገ የይዘት ትንተናና ግምገማ)**

በ

ጽጌ ታፈሰ

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ዶር ደጀኔ ለታ ______________ ፈታኝ ______________ ፊርማ

አቶ ማሞ ክፈሌ ______________ ፈታኝ ______________ ፊርማ

አቶ ጌታሁን አማረ ______________ አማካሪ ______________ ፊርማ

# ምስጋና

ጥናቱ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ረቂቁን በማንበብ ለእርማት የሚያገዙኝን ገንቢ አስተያየታቸውንና ምክራቸውን በመለገስ እርዳታቸው ላልተለየኝ አማካሪዬ ለአቶ ጌታሁን አማረ፣ ማበረታቻና ድጋፍ ላደረጉልኝ የትምህርት ክፍሉ ባልደረቦች፣ መጠይቅ በመሙላት ለተባበሩኝ መምህራን፣ ቃለ መጠይቅ በመመለስ ያልተቆጠበ እገዛ ላደረጉልኝ የመጻህፍቱ አዘጋጆች ባለውለታዎቼ ስለሆኑ ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

የሞራልና የማቴሪያል ድጋፉ ሳይለየኝ ከጎኔ በመሆን ለትምህርቴ መሳካት ያበረከተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ ለውድ ባለቤቴ ለአቶ ምንዳ ገብሬ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

# ማውጫ

ምስጋና

አጠቃሎ

ገፅ

## ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ ............................................

1.2 የጥናቱ ዓላማ............................................ 1

1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት........................................ 2

1.4 የጥናቱ ወሰን............................................ 3

1.5 ያጋጠሙ ችግሮች........................................ 4

## ምዕራፍ ሁለት

የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት

2.1 የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ምንነት................................ 5

2.2 የጽህፈት ክሂል............................................ 7

2.2.1 ስነልቡናዊ ባህርይ........................................ 7

2.2.2 ስነልሳናዊ ባህርይ........................................ 8

2.2.3 አእምሮታዊ ባህሪይ........................................ 8

2.2.4 ጽህፈትና ንግግር ........................................ 9

2.3 የጽህፈት ክሂል ይዘቶች........................................ 10

2.3.1 ከዓላማ ጋር ያላቸው ቁርኝት.................................. 10

2.3.2 ከስነዘዴ ጋር ያላቸው ትስስር.................................. 11

2.3.3 ከመነቃቃት ጋር ያላቸው ተዛምዶ ........................ 12

2.3.4 ጠቀሜታ ............................................ 13

2.4 የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ምርጫ.................................. 15

2.4.1 ተገቢነት............................................ 16

2.4.2 አስፈላጊነት............................................ 16

2.4.3 ዘላቂነት.................................................. 16
2.4.4 አስደሳችነት.............................................. 17
2.4.5 ለመማር ያላቸው አመቺነት.................................. 17
2.5 የጽህፈት ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት................................ 18
2.5.1 ተዋረዳዊ አደረጃጀት.......................................... 18
2.5.1.1 ተከታታይነት ............................................ 19
2.5.1.2 ተለጣጣቂነት.............................................. 20
2.5.2 ጎናዊ አደረጃጀት............................................. 22

ምዕራፍ ሦስት

የጥናቱ ዘዴ

3.1 የመረጃ ምንጮች.................................................. 27
3.2 የናሙና አወሳሰድ................................................ 28
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች...................................... 29
3.4 የመጠይቆች አዘገጃጀት........................................... 29

ምዕራፍ አራት

የመረጃ ትንተናና የጥናቱ ውጤት

4.1 የመረጃ ትንተና.................................................... 31
4.2 የጥናቱ ውጤት.................................................... 93

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያና የመፍትሔ ሃሣቦች

5.1 ማጠቃለያ.......................................................... 95
5.2 የመፍትሔ ሃሣቦች.................................................. 97
ዋቤ መጻህፍት
አባሪዎች

# አጠቃሎ (Abstract)

የዚህ ጥናት አላማ በአዲስ አበባ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ ለመጀመሪያ ደረጃ የሁለተኛው እርከን (5-8) በተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የጽህፈት ክሂል ይዘቶችን አደረጃጀት መተንተንና መገምገም ነው።

በዚህ አላማ መነሻነትም ጥናቱ በይዘት ትንተና የምርምር ስልት ተካሂዷል። መረጃዎቹም የተሰበሰቡት በይዘቶች ላይ ትንተና በማድረግ ፣የየክፍሉን መምህራን የጹሁፍ መጠይቅ በማስሞላትና ለመጻህፍቱ አዘጋጆች በቀረበ ቃለ መጠይቅ ነው።

መረጃዎቹም ከትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት መርሆች አኳያ ተተንትነዋል። በዚህም መሠረት በአራቱም ክፍሎች የጽህፈት ኪሂል ይዘቶችን አስመልክቶ የተለጣጣቂነት መስፈርት በአግባቡ ሥራ ላይ አለመዋሉና ለዚህም አብይ ምክንያት የሆነው ይዘቶቹ የተማሪውን ችሎታ የሚመጠኑ ሆነው አለመመረጣቸው መሆኑ ተደርሶበታል።

በነዚህና በሌሎች ዝርዝር ግኝቶች በመመርኮዝ ለወደፊቱ ይዘቶቹን የተማሪውን ችሎታ እንዲመጥኑ በማድረግ እና የአደረጃጀት መስፈርቶቹም ተጠብቀው ቢደራጁ ጥሩ ውጤት እንደሚያስገኙ ጥናቱ ይጠቁማል።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ትኩረት የጽህፈት ክሂል ይዘቶችን ከይዘት አደረጃጀት መርሆች አኳያ መገምገም ነው። ጥናቱም የተመሠረተው በአዲስ አበባ መስተዳደር ትምህርት ቢሮ ለሁለተኛው እርከን በተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መፃህፍት ላይ ነው።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የጥናቱ ዳራ ፣ ዓላማ ፣ አስፈላጊነት፣ ወሰንና በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ተካተዋል።

1.1 <u>የጥናቱ ዳራ</u>፣ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት መርሐ ትምህርትን መሠረት በማድረግ የሚዘጋጁ የትምህርት መማሪያዎች ናቸው። ቋንቋን ለመጠቀምም የመነሻ ጽሁፍ ሆነው ያገለግላሉ (Harmer1992) ።

የመማሪያ መጻህፍት ሲዘጋጁ ለዓላማው የሚስማሙ ይዘቶችን መርጦ ማደራጀት አንዱ የማይታለፍና አብይ ተግባር ነው። በዚህም መሠረት ለጽህፈት ክሂል ማዳበሪያነት የሚመረጡ ይዘቶች ተደራጅተው መቅረብ እንዳለባቸው አጠያያቂ አይሆንም። ምክንያቱም የይዘት አደረጃጀት ጥንካሬና ድክመት በመማር ማስተማር ብቃት ላይ አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ስለሚያደርስ ነው (Taba 1962, Tyler 1949) ።

በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉ የሀገር ውስጥ ጥናቶች የተማሪዎች የጽህፈት ክሂል በዝቅተኛና በአሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ተጠቁሟል። ለዚህም ምክንያት በማድረግ የልምምድ ጊዜ ማነስን ሰለሞን ተሰማ (1986) ፣ የፅሑፍ ቋንቋ ውስብስብነትን ስዩም ከበደ (1988) ፣ የመማሪያ መጻህፍት አቀራረብ ድክመቶችን አለማየሁ ፀጋዬ(1986) ፣ የችሎታ ማነስንና

የመማሪያ መጻህፍት አቀራረብብ ድክመቶችን አለማየሁ ፀጋዬ(1986) ፣ የችሎታ ማነስንና የዝንባሌ ማጣትን ክፍሌ ሐብተማርያም (1987) አቅርበዋል። በነዚህ ጥናቶች የጽህፈት ክሂልን ይዘቶች አደረጃጀት አስመልክቶ የተነሳ ነገር የለም። ስለዚህ የጽህፈትን ክሂል ከይዘቶች አደረጃጀት አኳያ ማጥናት የዚህ ጽሁፍ አብይ ጉዳይ ሆነ።

1.2 <u>የጥናቱ ዓላማ</u> ፤ የመማሪያ መፃህፍት በሚዘጋጁበት ጊዜም ሆነ ተዘጋጅተው በስራ ላይ ከዋሉ በኋላ በየጊዜው ሊገመገሙ ይገባቸዋል። ይህም ጠንካራና ደካማ ጎኖቹን ለመለየት ያስችላል። በዚህም መሠረት ይህ ጥናት ዋነኛ ዓላማው አድርጎ የተነሳው በአዲስ አበባ መስተዳደር ትምህርት ቢሮ በተዘጋጁት የመጀመሪያ ደረጃ የሁለተኛው እርከን የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ላይ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት ከትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት መስፈርቶች አኳያ መተንተንና መገምገም ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው።

1.2.1 የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹን ተዋረዳዊ አደረጃጀት መመርመር ይኸውም፤

1.2.1.1. ይዘቶቹ በአስፈላጊ ድግግሞሽ ቀርበዋልን?

1.2.1.2. ይዘቶቹ ከቀላል ወደ ከባድ በመሄድ ተደራጅተዋልን?

12.1.3. የቀደሙ ይዘቶች ለኋለኞቹ መሠረት ይሆናሉን?

1.2.1.4. የተመደበው ጊዜና የይዘቶቹ ብዛት ይመጣጠናሉን?

1.2.2. የፅህፈት ክሂል ይዘቶቹን ጎናዊ አደረጃጀተ መገምገም ይኸውም፤

1.2.2.1. የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ ከሌሎቹ ክሂሎች ጋር በመጣመር ቀርበዋልን?

1.2.2.2. የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ ከሌሎች የትምህርት ዘርፎች ጋር ተዋህደው ቀርበዋልን ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ መፈለግ

ነው።

ስለዚህ የጥናቱ አብይ ዓላማ የሚያስገኘውን ውጤት መሠረት በማድረግ ከጽህፈት ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት አኳያ ለማጥናት ነው።

1.3 **የጥናቱ አስፈላጊነት፤** የመማሪያ መጻህፍት በየጊዜው ሊገመገሙና ሊሻሻሉ እንደሚገባቸው ከላይ ለመግለፅ ተሞክሯል። ለዚህም የተለያዩ ምሁራን የመገምገሚያ ነጥቦችን ማዘጋጀት እንደሚቻል ይመክራሉ። ከነሱም መካከል Reid ( 1993፤99) "ከጽህፈት ክሂል አኳያ የይዘቶቹን ተዋረዳዊና ጎናዊ አደረጃጀት መገምገም አንድ ስነትምህርታዊ ፋይዳ ይገኝበታል" ሲሉ ur (1996፤86) ደግሞ "መጻህፍትን ለመገምገም የይዘቶችን ተከታታይነት ፤ ተለጣጣቂነትና ውህደት ማጥናት አስፈላጊ የሆነ ትምህርታዊ ጉዳይ ነው።" ይላሉ። ሁለቱም ሊቃውንት የይዘት አደረጃጀት ጥናትን ጠቃሚነት ይጠቁማሉ።

የጽህፈት ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት ስለቋንቋ ባህርይና ስለጽህፈት ትምህርት አቀራረብ በሚኖር ግንዛቤ ላይ ሊመሠረት ይገባዋል። ምክንያቱም የቋንቋ ትምህርት ይዘት በቋንቋ ባህርይ ላይ ይመሠረታልና ነው (Hutchenson & wateers 1994) ።

ስለዚህ የይዘት አደረጃጀትም ከየክሂሎች አኳያ ሊጠና ይገባዋል። በመሆኑም ይህ ጥናት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል ተብሎ ተገምቷል።

ክሂሎችን ነጣጥሎ ማቅረብ አስቸጋሪ መስሎ ቢታይም እያንዳንዱ ክሂል ደግሞ የተለየ ትኩረትን ይፈልጋል። በዚህም መሠረት ይህ ጥናት በጽህፈት ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት ዙሪያ የመደረጉ አስፈላጊነት የሚያጠያይቅ አይሆንም።

ከጥናቱ አስፈላጊነት ጎን ለጎንም የሚያስገኛቸውን ጠቀሜታዎች በሚከተለው መልክ መዘርዘር ይቻላል።

1.3.1.የመማሪያ መፃህፍት ሲዘጋጁም ሆነ ሲሻሻሉ የይዘት አደረጃጀት ትኩረት ሊያገኝ የሚገባው ነጥብ ሆኖ ሊጠቅም ስለሚችል፤

1.3.2. በቋንቋ ትምህርት ልዩ ልዩ ክሂሎች አኳያ ለሚደረግ ምርምር አደረጃጀትን አስመልክቶ የመነሻ ሐሳብ ሊሰጥ ስለሚችል፤

1.3.3. በተለያዩ ክፍሎች የመማሪያ መጻህፍት ላይ ለሚደረግ ጥናት ከይዘት አደረጃጀት አኳያ የመንደርደሪያ ሐሳብ ሊያስጨብጥ ስለሚችል፤

1.3.4. ለመማሪያ መፃህፍት አዘጋጆች ቀጥተኛ ምጋቤ ምላሽ በመሆን ሊጠቅም ስለሚችል፤ የጥናቱ አስፈላጊ መሆን ታምኖበታል።

1.4 <u>የጥናቱ ወሰን</u> ፤ የዚህ ጥናት አድማስ በአዲስ አበባ መስተዳደር ትምህርት ቢሮ በሁለተኛው እርከን በማገልገል ላይ ባሉት የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ላይ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት ላይ ብቻ የሚያተኩር ነው። የእርከኑን መጻህፍት (ከ5ኛ -8ኛ) በሙሉ ለማካተት የተፈለገበትም ምክንያት የአንዱን ክፍል ብቻ በተናጠል ማየቱ ጥናቱን ምሉዕነት ያሳጣዋል በሚል ፍራቻ ነው። በተጨማሪም በአዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በሁለት እርከኖች መከፈሉ የሚታወቅ ነው። ይኸውም ከ 1-4 የመጀመሪያው እርከን ከ 5-8 ደግሞ ሁለተኛው እርከን ናቸው። በፖሊሲው መሠረት የሁለተኛውን እርከን የፈፀመ ተማሪ ያሳያል ተብሎ የሚታሰበው የባህርይ ለውጥ እንደሚከተለው ተቀምጧል። "የዚህ ሳይክል ትምህርት ለአጠቃላይና ለተከህኖ ትምህርት ተገቢ የሆኑ ዕውቀትን፤ ችሎታን ፤ ክሂሎትንና ዝንባሌን ለመፍጠር መሠረት የሚጥል ይሆናል" ይላል። (አዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ 1985፥4 )

በፖሊሲው መሠረትም አጠቃላይ ትምህርት ሁሉን አቀፍ የዕውቀት ክፍሎችን እንደሚያካትት ለማወቅ ተችሏል። ከዚህም የሁለተኛውን እርከን ያጠናቀቀ ተማሪ በቋንቋው የትምህርት ዘርፍም ለመካከለኛው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ደረጃ የሚያሸጋግረው እውቀት ሊጨብጥ እንደሚገባው ያስገነዝባል። ስለሆነም የጽህፈት ክሂሉን በደረጃው እንዲያዳብር የተመረጡለትን ይዘቶች አደረጃጀት በእርከኑ ውስጥ ለማየት ታስቧል።

በጥናቱም ለማመሳከሪያነት እንዲያግዙ የመምህሩ መምሪያና መርሐ ትምህቱ ይታያሉ እንጂ የትንታኔው ትኩረት በመማሪያ መጻህፍቱ ላይ ብቻ ይሆናል።

በተጨማሪም የይዘት አደረጃጀት ሲባል የይዘት ምርጫንም እንደሚያካትት ይታመናል (Nunan 1988) ። ስለዚህ ለዚህ ጥናትም የይዘት ምርጫን ማንሳት አግባብነት ስለሚኖረው ከጽህፈት ክሂል ጋር በተያያዘ ሁኔታ መጠነኛ ትንታኔ ይሰጥበታል።

1.5 <u>ያጋጠሙ ችግሮች</u> ፤ በጥናቱ ክንውን ወቅት ካጋጠሙ ችግሮች መካከል የሚከተሉት ናቸው።

- አንዳንድ መምህራን መጠይቁን ለመሙላት ፈቃደኛ አለመሆናቸው ፤
- አንዳንድ የመጻህፍት አዘጋጆች መረጃ ለመስጠት ባለመፈለግ የመሰላቸት ባህርይ ማሳየታቸው፤
- የተወሰኑ የመጻህፍት አዘጋጆች የአድራሻ ለውጥ በማድረጋቸው ለማግኘት አለመቻሉ።
- ፈቃደኛ የሆኑት መረጃ ሰጪዎች ደግሞ በነበረባቸው የጊዜ እጥረት የጥናቱን ጊዜ መሻማታቸው በመረጃ ስብሰባ ወቅት የተከሰቱ ችግሮች ነበሩ።

# ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

በዚህ ምዕራፍ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ሥራዎች ይቀርባሉ። በዚህም መሠረት ስለቋንቋ ትምህርት ይዘቶች አጠቃላይ ባህርይ ፣ ስለጽህፈት ክሂል ይዘቶች ምርጫና አደረጃጀት የሚያመለክቱ ጽሁፎች ይቃኛሉ።

2.1 <u>የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ምንነት</u> ፣ አንድ የቋንቋ ትምህርት የተነደፈለትን ዓላማ ለማዳበር ልምምድ እንዲደረግባቸው ተመርጠው የሚቀርቡ የቋንቋ አካላት ይዘቶች ይባላሉ። ቋንቋ ስፋትና ውስብስብነት ያለው የመግባቢያ መሣሪያ በመሆኑ የተወሰኑትን መርጦ በየደረጃው በይዘትነት ማቅረብ ግድ ነው። ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት ፍሬያማ ውጤት እንዲገኝ ከተፈለገ ቋንቋውን ከፋፍሎ ማቅረብ ያስፈልጋል። እነዚህም ክፍልፋዮች በቋንቋው ቅርፅና አጠቃቀም የሚገልፁ ይዘቶች ናቸው (Cunningsworth 1995) ። በዚህም መሠረት ይዘቶች የአንድን ቋንቋ ስርዓትና አጠቃቀም አጣምረው የሚይዙና የተማሪውን ተግባባታዊ ክሂል ከፍ የማድረግ አቅም እንደሚኖራቸው የሚገመቱ መማሪያዎች መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል። የትምህርት ባለሙያዎችም ስርዓቱንና አጠቃቀሙን በማዋሃድ ለይዘቶቹ ስነትምህርታዊ መልክ መስጠት ይጠበቅባቸዋል።

የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች የትምህርት ይዘቶች አካል እንደመሆናቸው ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር የሚመሳሰሉባቸው ነጥቦች ሲኖሯቸው በቋንቋ ትምህርትነት ባህርያቸው ደግሞ የሚለያዩባቸው ሁኔታዎች አሏቸው። በዚህም መሠረት የትምህርት ይዘቶች ከተለያዩ የመማር ማስተማር ሁኔታዎች ጋር ተዳምረው ዓላማን ከግብ ሊያደርሱ

የሚችሉ ፋይዳ ያላቸው የትምህርት ግብአቶች መሆናቸውን የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችም የሚጋሩት ይሆናል። የሌሎች ትምህርት ይዘቶች ሌሎች ፅንሰ ሐሳቦች ሲሆኑ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ግን የራሱ የቋንቋው አካላት መሆናቸው ደግሞ የልዩነት ነጥባቸው ነው።

የትምህርት ይዘቶች የዓላማ መተርጎሚያዎችና የአእምሮ ብቃትን በማዳበር ረገድ የበጎ ባህርይ ለውጥ የሚያስገኙ የትምህርት ፋይዳዎች መሆናቸውን መረዳት አስፈላጊ ነው። ተማሪውን ወደ ተፈለገው ዓላማ ማድረስ የሚቻለው የልምምድ ዕድል ሊያስገኙለት በሚችሉ የትምህርት ይዘቶች አማካይነት ነው። የትምህርት ይዘቶች በራሳቸው ግቦች ሳይሆኑ ቁምነገር አዘል የመለማመጃ መሣሪያዎች ናቸው ( Ponser እና Rudentsky 1980 Tyler 1949) ። በዚህ ሐሳብ መሠረትም የትምህርት ይዘቶች ወደ ዓላማ ማነጣጠር የሚገባቸው የትምህርት ገፅታዎች መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል።

የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ምን መማር? የሚለውን ሐሳብ ይገልፃሉ ለመማር አመቺ እንዲሆኑም በተወሰነ አደማስና ጥልቀት መሠረታዊ የቋንቋ ትምህርት ፅንሰሐሳቦችና የንዑሳን ክሂሎች መለማመጃዎች በመሆን ደቀው ይቀርባሉ። ለምሳሌ፤

ለማዳመጥ ክሂል - መረጃን ለመሻት ማዳመጥ

ለንግግር ክሂል - የውይይት ስርዓት

ለንባብ ክሂል - የአስሳ ንባብ

ለጽህፈት ክሂል - የደብዳቤ አፃፃፍ ይዘቶች ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ።

የጥናቱ ትኩረት በጽህፈት ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት ላይ በመሆኑ የሚቀጥለው የጽሁፍ ክፍል ከጽህፈት ክሂል ጋር ተዛምዶ ያላቸው ጉዳዮች የሚቃኙበት ነው።

2.2 <u>የጽህፈት ክሂል</u> ፣ ጽህፈት ለንግግር ድምፆች በተወከሉ ምልክቶች አማካይነት ሐሳብን በወረቀት ላይ ለመግለፅ በማስቻሉ ለተማረ ሰው እንደ አንድ ምልክት የሚቆጠር ሰው ሠራሽ መገልገያ ነው። ክሂሉን በማስተማር የማዳበሩ ተግባር የሚመለከተውም ትምህርት ቤትን ብቻ ነው (Raimes 1983 Rivers 1981 Oller 1979) ።

ጽህፈት የዕውቀትና የታሪክ መመዝገቢያ በመሆኑ ሊማሩት የሚገባ ጠቃሚ ክሂል ነው። Reid ( 1993፣21) " እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ጽህፈትን ማስተማር ማለት መልመጃዎችን ማሠራትና የቃል ጽህፈት ነበር ፤ በዘመናችን ግን ጽህፈት ተግባባታዊና አእምሮታዊ ክሂልን ማበልፀጊያ ሆኖ ተገኝቷል።" በማለት ክሂሉን መማር ሊያስገኝ የሚችለውን ከፍተኛ ጠቀሜታ ይገልፃሉ።

ጽህፈት ባሉት ባህርያቱ የተነሳ በቀላሉና በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊዳብር የሚችል ክሂል ባለመሆኑ የዕድሜ ልክ ጉዞ ነው (Barr እና Barbara 1997) ። በዚህም መሠረት ሰፊ የልምምድ ጊዜ ስለሚያስፈልገው ጊዜ-ፈጅ ክሂል ነው ማለት ይቻላል። ሌሎቹ ጽህፈትን አስቸጋሪ የሚያደርጉት ባህርያቱ ደግሞ ስነልቡናዊ ፤ ስነልሳናዊና አእምሮታዊ ገፅታዎቹ ናቸው። (Reid 1993 , Hedge 1988, Raimes 1983, Pincas 1982)

2.2.1 <u>ስነልቡናዊ ባህርይ</u> ፤ በጽህፈት ክንውን ወቅት አንባቢን ማሰብ የማይቀር ተግባር ነው። መልዕክቱ ለአንባቢው እንዲደርሰው ለማድረግ ፀሐፊው ይጨነቃል። Hedge ( 1988:5) " የጽህፈት ትምህርት ክፍለ ጊዜ የተማሪዎች ቁናቁና መተንፈሻ ፤ እግራችውን ማፍተጊያና እርሳሳችውን ማኘኪያ የስቃይ ጊዜ ነው።" በማለት

ጽህፈት በቀላሉ የሚታይ ክሂል አለመሆኑን ይገልፃሉ። ይህም ጽህፈት ባለው ስነልቡናዊ ባህርይው ምን ያህል አስጨናቂ እንደሆነ ያስገነዝባል።

2.2.2 <u>ስነልሳናዊ ባህርይ፣</u> ስነልሳን ቋንቋ የሚጠናበት ሳይንስ በመሆኑ የአንድ ቋንቋ ውስጣዊና ውጫዊ ገፅታ ይመረመርበታል። በጽህፈት ክሂል ረገድም የስነልሳን እውቀት አስፈላጊነት ጥያቄ ውስጥ አይገባም። ምክንያቱም ሐሳብን በጽህፈት አማካይነት አሻሚነት ሳይኖረው መግለፅ የሚቻለው የቋንቋውን መዋቅር በማጥናት በመሆኑ ነው። ተቀባይነት ያለው የሐሳብ አስዳደር እንዲገኝ የቋንቋን ህግጋት ማወቅ ያስፈልጋል። ስለዚህ የቋንቋን ስርዓት ከአጠቃቀሙ ጋር አስማምቶ በማቅረብ በጽሁፍ መግባባት ሊገኝ ይችላል። በጽሁፍ ውስጥ የተዋጣ ተግባቦትን ለማግኘት በንግግር ውስጥ አልባሌ መስለውን የምናልፋቸውን መዋቅሮች ሳይቀሩ ማጥናት ይገባናል (Hedge1988) ።

2.2.3 <u>አእምሮታዊ ባህርይ፣</u> ጽህፈት የአእምሮን እንቅስቃሴ የሚጠይቅ በመሆኑ አእምሮታዊ ባህርይው ነው። የጽሁፍ ስራ የግንዛቤን መዳበር ይፈልጋል። Moore(1995:13) " መፃፍ ማለት ማሰብ ማለት ነው።" ይላሉ። ከዚህም ለመረዳት የሚቻለው በመጠኑም ቢሆን ሳይታሰብበት የሚከናወን የጽህፈት ተግባር አለመኖሩን ነው። የጽህፈት እውቀት እጅን ዓይንንና አእምሮን በማስተባበር በተገቢ የድምፃዊ ምልክት ወኪሎች አማካይነት የግል ወይም የጋራ ገጠመኙን የማካፈል ችሎታን የሚጠይቅ ተግባር ነው (Reid 1993) ።

ስለዚህ ጽህፈት ብዙ ማሰላሰልንና ከራስ ጋር መሟገትን ይጠይቃል የመማሪያ መጻህፍት አዘጋጆችም እነዚህ ባህርያቱ በክሂሉ ላይ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ ከግምት ውስጥ በማስገባት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶቹን መምረጥ ይገባቸዋል የሚል እምነት አለ።

2.2.4 <u>ጽህፈትና ንግግር</u> ፦ሁለቱ ክሂሎች የአፍልቆት ክሂሎች በመሆናቸው ቢመሳሰሉም በየግል ባህርያቸው ደግሞ የሚለያዩባቸው ነጥቦችም አሏቸው። በዚህ ንዑስ ክፍልም የሁለቱን የልዩነት ነጥቦች ማንሳቱ ስለጽህፈት ክሂል ሰፋ ያለ ግንዛቤ ሊያስጨብጥ ይችላል በሚል ግምት እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሀ. የጽህፈት ትምህርት የሚገኘው ከትምህርት ቤት ሲሆን ንግግር ግን ያለ ትምህርት ይለመዳል

ለ. ጽሁፍ ሰው ሰራሽ ሲሆን ንግግር ግን ተፈጥሮአዊ ነው

ሐ. ጽህፈት ከንግግር የበለጠ ለቴክኖሎጂ ዕውቀት ማስተዋወቂያ የሚውል ወሳኝ መሣሪያ ነው።

መ. ጽህፈት በአብዛኛው ከንግግር የበለጠ አዝጋሚ ነው።

ሠ. ጽህፈት ታርሞ የመቅረብ ዕድል ያለው ሲሆን ንግግር ግን እየተከወነ ስለሚታረም ድግግሞሽ ይበዛበታል። ስለዚህ የጽህፈት ቋንቋ የመረጃ እምቅነት ያለው ሲሆን የንግግር ግን ዘርዛራ ነው።

ረ. ንግግር በሰውነት እንቅስቃሴ የሚደገፍ ሲሆን ጽህፈት ግን በአውድ መቅረብን ይፈልጋል።

ሰ. ንግግር ያለ አድማጭ አይከወንም ጽሁፍ ግን የአንባቢውን መኖር አይጠይቅም

ሸ. ጽህፈት በመደበኛ ቋንቋ መጠቀምን ሲጠይቅ ንግግር ግን በተለያዩ ዘዬዎች መጠቀምን አያግድም

ቀ. ለጽሁፍ የሚውሉ ቃላት ረቂቅነት ያላቸውን ጉዳዮች የማሳየት ኃይል እንዲኖራቸው ከሚያስችል ድባብ ጋር የተያያዙ ሲሆኑ ንግግር ግን ወዲያው እንደመጣም ሊቀርብ የሚችል ነው።

በ. ጽህፈት ከንግግር የበለጠ ዘላቂነት ያለው የትምህርት ምንጭ ነው ( Ur 1992 Hedge 1988 Byrne 1982 Pincas 1982) ።

በተጨማሪም በንግግር ሊገለፅ የሚችል ሐሳብ ሁሉ በጽሁፍም መገለፅ መቻል እንደሚገባው ማወቅ ያስፈልጋል። ንግግር የወዲያውነት ባህርይ ስላለውና የሰው ልጅ የማዳመጥ ችሎታው ደግሞ ውስን በመሆኑ መረጃን ዘላቂነት ባለው ሁኔታ በማስተላለፍ ረገድ ሁለቱ ልዩነት አላቸው። ስለዚህ የመማሪያ መጻህፍት አዘጋጆች ይዘቶችን ለመምረጥ ስለጽህፈት ክሂል ባህርያት ግንዛቤ መጨበጥ አለባችው። የጽሕፈትን ባህርያትና ጠቀሜታ መግለፅ መቻል መርሐትምህርትን እንደመቅረፅ ሊቆጠር ይችላልና (Oller 1979) ።

2.3 <u>የጽህፈት ክሂል ይዘቶች፣</u> ለጽህፈት ክሂል ዓላማ የሚመረጡ የቋንቋ አካላት ናችው። እንደሌሎቹ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ሁሉ በቋንቋ ስርዓትና አጠቃቀም ይገለፃሉ። የጽህፈትን ትምህርትና የክሂሉን ባህርይም መሠረት ያደርጋሉ።

ተማሪው በጽሁፍ ሊኖረው የሚገባውን ተግባቦታዊ ክሂል ከፍ እንዲያደርግ የማህበረሰቡን የቋንቋ አጠቃቀም ከቋንቋው ስርዓት ጋር አጣምሮ ማጥናት አለበት። ለምሳሌ የዓረፍተ ነገር አወቃቀር በጽህፈት የቋንቋውን ስርዓት የሚያለማምድ ይዘት ሲሆን ተረትና ምሳሌ ደግሞ ቋንቋውን ያለማምዳል። በዚህም ስርዓቱና አጠቃቀሙ ተደጋግፈው የጽህፈትን ክሂል የማሳደግ ብቃት ይኖራችዋል የሚል እምነት አለ።

2.3.1 <u>ከዓላማ ጋር ያላቸው ቁርኝት</u> ፣ የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማ ክሂሎችን ማዳበር ነው። የመማሪያ መጻህፍት አዘጋጆችም ዓላማውን መሠረት አድርገው ለየክሂሎቹ ተስማሚነት አላቸው የሚሏችውን ይዘቶች ይመርጣሉ። በጽህፈት ክሂል አኳያም የተጣራ የእጅ ጽህፈት ፣ የሆሄያት ትክክለኛ አገባብ ፣ ስርዓተ ነጥቦችና ተቀባይነት ያለው ሰዋሰውና የቃላት ምርጫ ትኩረትን ከሚሹ ይዘቶች ይመደባሉ ( Ur 1996) ።

የጽህፈት ክሂል ግቡን ይመታ ዘንድ ተማሪዎቹ በየደረጃቸው ምን ምን የቋንቋ አካላትን ሊማሩ ይገባቸዋል? የሚለው ጥያቄ በቅድሚያ መመለስ አለበት፡፡ ለዚህም የተማሪው ማንነት ፣ የሚማርበት ዓላማ ፣ የሚማርበት የጊዜ መጠን ፣ ያለፈው የቋንቋ ትምህርት ዳራው ፣ የቋንቋው ባህርይ ፣ የተማሪውና የማህበረሰቡ ፍላጎት በወጉ ሊጤኑ የሚገባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

የትምህርት ዓላማ ይዘትን መምረጫ አንድ መስፈርት ነው፡፡ ስለዚህም ይዘት ከዓላማ የሚመነጭ ነው ማለት ይቻላል ( Corder 1973 Tyler 1949) ፡፡ በዚህም መሠረት ይዘትና ዓላማ እንደማይነጣጠሉ መገንዘብ አያዳግትም፡፡ ተማሪው ለምን እንደሚማር ከታወቀ በኃላ ያለፈውን ዳራውን በመመርኮዝ ምን መማር እንዳለበት ይወሰናልና ፡፡ ስለዚህ ዓላማንና ይዘትን እንደ አንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ማየት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ይዘቶች ወደ ዓላማ የሚያደርሱ መለማመጃዎቹ በመሆናቸው ያለ ይዘት ዓላማ ያለ ዓላማ ደግሞ ይዘት አይታሰብምና ነው፡፡

2.3.2 ከስነዘዴ ጋር ያላቸው ትስስር ፣ የማስተማሪያ ስነዘዴ ለትምህርትነት በሚቀርበው ጉዳይ ባህርይ የሚወሰን የማስተማሪያ መንገድ ነው፡፡ መንገዱም ወደ ግብ የሚጓዙበት ነው፡፡

በየዘመናቱ የቋንቋን ልዩ ልዩ ባህርያት መሠረት ያደረጉ ስነዘዴዎች ተቀርፀው ግልጋሎት ላይ ውለው እንደነበር የሚታወቅ ነው፡፡ ለአብነት ያህልም ጥንታዊው የሰዋሰውና ትርጉም ዘዴ በሰዋሰው ህግጋት የቃል ጥናት ላይ የተመሠረተ ሲሆን አዳምጦ የመመለስ ዘዴ ደግሞ የተባለውን መልሶ በማለት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ አብዛኞዎቹ ለጽህፈት ክሂል የጠቀሜታውን ያህል ትኩረት የሚሰጡ አልነበሩም፡፡ ዘመናዊው ተግባቦታዊ ስነዘዴ ግን ጽህፈትም ከሌሎቹ ክሂሎች እኩል የሆነ ድርሻ ሊኖረው እንደሚገባ ያሳያል፡፡ ስለዚህ

ተማሪው በግልም ይሁን በቡድን የጽህፈትን ክሂል በሚያለማምዱት ይዘቶች አማካይነት ክሂሉን ለማዳበር ጥረት ሊያደርግ ይገባዋል የሚል አስተሳሰብን መሠረት ያደርጋል።

ስለ ይዘትና ስነዘዴ Corder (1973:5) ሲገልፁ " ስነዘዴ ከይዘት ይፈልቃል" ይላሉ ይህም የሚያመለክተው ለሚመረጠው የጽህፈት ክሂል ይዘት የሚመች ስነዘዴ ሊመረጥ መቻሉን ነው። ስነዘዴ የተባለ ሁሉ የተዋጣለት ባለመሆኑ እንደይዘቱና እንደሁኔታው መራርጦ መጠቀም ተመራጭ አካሄድ ነው (Rivers 1988) ።

በሌላ መልኩ ስነዘዴ በተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ላይ በጎም ይሁን መጥፎ ሁኔታ ሊያሳድር ይችላል። ስለዚህ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ቋንቋውን እንዲጠቀሙበት በሚያስችላቸው መንገድ ሊቀርብላቸው ይገባል ማለት ነው።

2.3.3 <u>ከመነቃቃት (Motivation)ጋር ያላቸው ተዛምዶ</u> ፣ ቋንቋን በመማርና ማስተማር ሂደት የተማሪው መነቃቃት ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽዖ አለው። የተነቃቃ ተማሪ ትምህርቱን በመቀበል ረገድ ካልተነቃቃው ተማሪ ይልቃል (Cunningsworth 1995 Harmer 1991) ። ከዚህም መነቃቃት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ቁልፍ ጉዳይ ሆኖ ሊጠቀስ ይችላል።

የተማሪውን መነቃቃት ለመጠበቅ በትምህርቱ ይዘት ምርጫ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ለጽህፈት ክሂል የሚመረጡትን ይዘቶች ተማሪው በደረጃው ሊሠራቸው የሚችላቸው ከሆኑ መነቃቃትን ይጨምሩለታል። በዝቅተኛ ደረጃ ለሚገኝ ተማሪ የስራ ደብዳቤ እንዲያዘጋጅ ከመጠየቅ ይልቅ ለጓደኛህ ደብዳቤ ፃፍለት ቢባል የበለጠ ሊነቃቃ ይችላል። ስለዚህ የይዘቶች ተማሪውን አለመመጠን መነቃቃትን እንደሚቀንስ መገመት ይቻላል።

ከላይ በዝርዝር ለማሳየት የተሞከረው ይዘቶች ከዓላማ ከስነዘዴና ከመነቃቃት ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው መሆኑን ነው። እያንዳንችውም የሚደጋገፉ ሆነው ይታያሉ። የመነቃቃትና የስነዘዴ መጓደል ዓላማን ሊያደናቅፍ ይችላልና ። ስለዚህ የመማሪያ መጻህፍት አዘጋጆች የጽህፈት ክሂል ይዘቶችን በመምረጥና በማደራጀት ወቅት ልብ ሊሏቸው ያስፈልጋል። ቀጥሎ ደግሞ የጽህፈት ክሂል ይዘት ከመማሪያ ግብአትነት ባሻገር ምን ምን ጠቀሜታዎች እንዳሏቸው ለማሳየት ይሞከራል።

2.3.4 <u>ጠቀሜታ</u> ፤ ለጽህፈት ክሂል የሚመረጡ ይዘቶች እንደፋብሪካ ጥሬ ዕቃ ሊቆጠሩ የሚችሉ የመማሪያ መሣሪያዎች ናቸው ማለት ይቻላል። የትምህርት ይዘቶች ያላቸውን ጠቀሜታ Tyler ( 1949 : 68-83) በመዘርዘር ያቀርባሉ። በዚህ ጽሁፍም ከዓላማው ጋር በማጣጣም ቀጥለን ለማየት እንሞክራለን።

ሀ. <u>የትምህርት ይዘቶች የማሰብን ክሂል ስለሚያበለፅጉ ተጠያቂያዊ አስተሳሰብ እንዲዳብር ያግዛሉ፤</u> ጽሕፈት ሐሳብን በወረቀት ላይ ማቅረቢያ ክሂል ነው። የሐሳብ አደረጃጀትም አንድ የክሂሉ ይዘት ሆኖ የሚቆጠር ነው። ይህም ተጠያቃዊ አስተሳሰብን በእጅጉ የሚሻ ነው። በአነስተኛ የጽሕፈት ስራም ቢሆን የሐሳብ አደረጃጀት ትኩረት የሚፈልግ ጠቃሚነት ያለው ይዘት ነው ( Raimes 1988) ።

የሀሳብ አደረጃጀት ተጠየቃዊ አስተሳሰብን ከፍ ሊያደርግ ስለሚችል የማሰብ ክሂልን ያበለፅጋል ማለት ይቻላል። ተማሪው ምን ? ለማን? ለምን? እንዴት? እፅፋለሁ እያለ ሐሳቡን ያውጠነጥናል። በመጨረሻም የመሰለውን መርጦ ይፅፋል። እየደጋገመም ይለማመዳል።

ለ. የትምህርት ይዘቶች ሀሳቦችን ፤ ንጽፈሐሳቦችን ማጠቃለያ የሚሆኑ ሐሳቦችን ፤ ልምዶችን ፤ እውነታዎችንና ስያሜዎችን ሳይቀሩ በመረጃነት ያስጨብጣሉ፤ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች በጽህፈት ቅርፅና ይዘት ላይ ሊያተኩሩ ይችላሉ ስለ አንቀፅ አወቃቀር የቀረበ ይዘት የአንቀፅ አፃፃፍ ሀሳቦችን ያለማምዳል። የዘይቤዎችን አጠቃቀም የተመለከተ ይዘት ንድፈሐሳብን ያስጨብጣል። ስርዓተ ነጥብም የራሱ መመሪያዎች ስላሉት ለምሳሌነት የሚበቃ ይዘት ነው።

ሐ. የትምህርት ይዘቶች በራሳቸው እሴቶች ሳይሆኑ ተተግባሪዎች ናቸው፤ የትምህርት ይዘቶች ጠቀሜታ የሚስተዋለው በተግባር ላይ ከዋሉ በኃላ ነው። የጽህፈት ክሂል ይዘቶችን በመሸምደድ ብቻ ወደ ዓላማው መድረስ አይቻልም። በልምምድ ብዛትም ንዑስ ክሂል እየሆኑ ይዳብራሉ።

መ. የትምህርት ይዘቶች ማህበራዊ አመለካከትን ያሰፋሉ፤ ቋንቋ የህብረተሰብ ማጥኛ መሣሪያ እንደመሆኑ ተማሪው የቋንቋ ችሎታው እየዳበረ በሄደ መጠን አመለካከቱም እየሰፋ ሊሄድና ግንዛቤው ሊጨምር ይቻላል። ለዚህም ይዘቶች ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። የጽህፈት ክሂሉ በይዘቶቹ አማካይነት ከዳበረ በሚያስተላልፈው መልዕክት የአመለካከቱን ደረጃ ለመገመት ይቻላል።

ሠ. የትምህርት ይዘቶች ዝንባሌን ይፋ ያወጣሉ ፤ የትምህርት ይዘቶች የተደበቀን የተማሪ ዝንባሌ ሊቀሰቅሱ ይችላሉ ። የአንዳንድ ተማሪዎች የስነጽሁፍ ተውህቦ በጽህፈት ክሂል ይዘቶች አማካይነት እየዳበረ ሊሄድ ይችላል። ይዘቶቹ ለዝንባሌው ይፋ መውጣት የሚኖራቸው አስተዋጽኦ ቀላል ሆኖ የሚታይ አይደለም። በዚህ ጥናት አቅራቢም የብዙ ዓመታት የማስተማር ልምድ የተገኘው ግንዛቤም ይህንኑ የሚደግፍና የሚያጠናክር ነው።

በአጠቃላይ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ሰፋት ያለው መሠረት የያዙ የቋንቋ ገፅታዎች መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል። ስለዚህም በአመራረጣቸው ወቅት ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ የጽህፈት ክሂል ይዘቶችን እንዴት መምረጥ እንደሚገባ ለመቃኘት እንሞክር።

2.4 <u>የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ምርጫ</u> ፣ ከአንድ ቋንቋ አካላት ውስጥ የተወሰኑት ተመርጠው በይዘትነት እንደሚቀርቡ ቀደም ተብሎ ተገልጿል። የመማሪያ መጻህፍት አዘጋጆችም ለጽህፈት ክሂል የሚውሉትን ይዘቶች በተማሪው ደረጃ አመጣጥነው እንዴት መምረጥ እንዳለባቸው ሊያጤኑ ይገባቸዋል። የቋንቋ ትምህርት ይዘት ምርጫ ስለ ቋንቋ ባህርይና ትምህርት ባለ ንድፈ ሐሳባዊ አመለካከት ይወሰናል (Nunan 1988) ። በዚህም መሠረት የትኞቹ የቋንቋ አካላት ለየትኞቹ ተማሪዎች ይቅረቡላቸው የሚለውን ለመመለስ የተማሪዎቹን የቋንቋ ችሎታ፤ ፍላጎት ፤ ዝንባሌና እውቀት በጥንቃቄ መረዳት ያስፈልጋል። በጽህፈት ክሂል ረገድም ስለ ጽህፈት ትምህርትና ባህርይ አስቀድሞ መገንዘብ ይዘቶቹን በመወሰን ረገድ የሚጫወተው ሚና ቀላል ሆኖ አይገመትም። አምደስላሴ ገብረክርስቶስ (1985 ፣ 69) " ይዘቶች ሲመረጡ የተማሪውን ውስጣዊ ጥንካሬ በመገንባት ለዓለምና በይበልጥም ለአካባቢው የሚኖረውን አተያይ የሚያሻሽሉት ላይ ማተኮር ያስፈልጋል።" በማለት የይዘት ምርጫ እልፍ ብሎ ማሰብን የሚጠይቅ ተግባር መሆኑን ይገልፃሉ። ስለዚህ ለጽህፈት ክሂል የሚመረጡት ይዘቶችም ተማሪው በደረጃው ሐሳቡን በሚገባ ለመግለፅ የሚያስችሉት ሊሆኑ ይገባቸዋል።

የትምህርት ይዘቶች ምርጫ የሚያስፈልገው የክሂሉን ትምህርት በማቅረብ ረገድ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ነው። የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ሲመረጡም ከተማሪዎቹ ስሜትና ፍላጎት ጋር ያላቸው ስምረት ፣ ተግባራዊ ጠቀሜታቸው ፣ ለመማር ያላቸው አመቺነት ፣ ከዓላማ ጋር ያላቸው ቁርኝትና ሰፋት ጥልቀታቸው ሊመረመሩ ይገባቸዋል። ለበርካታ

ምሁራን የጋራ የሆኑት የይዘት መምረጫ መስፈርቶች ተገቢነት አስፈላጊነት ፤ ዘላቂነት፤ አስደሳችነትና ለመማር ያላቸው ምቹነት ናቸው ( Cunningsworth 1995 ur 1996 Nutta!! 1983 Tyle 1949) ።

በመቀጠል እነዚህን ለይዘት መምረጫ የሚያገለግሉ መስፈርቶች ከጽህፈት ክሂል ይዘቶች አኳያ ለማየት እንሞክር።

2.4.1. <u>ተገቢነት</u> ፤(appropratness) ለክሂሉ የተነደፈውን ዓላማ ግብ በማስመታት የባህርይና የአሰራር ለውጥ ለማስገኘት መለማመጃ እንዲሆኑ ማድረግ ተገቢነትን ያሳያል። አንድን ይዘት ተማሪው በተግባር ሊያውለው የሚችለው ካልሆነ ዋጋቢስ ነው። የፊደላትን ቅርፅ ለይቶ ላላወቀ ተማሪ አንቀፅ እንዲፅፍ የሚያመለክት ይዘት ተገቢነት የሌለው የይዘት ምርጫ ነው። ስለዚህ ተማሪው በጽህፈት ሊኖረው የሚገባውን መግባባት ያሳድጉለት ዘንድ የሚመረጡለት ይዘቶች ከችሎታውና ከትምህርቱ ዓላማ ጋር የተገናዘቡ መሆን አለባቸው።

2.4.2. <u>አስፈላጊነት</u>፣ የሚመረጠው ይዘት ተማሪው እንዲያውቀው የተፈለገውን ነገር ለመጨበጥ ያስችለዋልን የሚለውን ጥያቄ የሚመለከት ነው። የተማሪው ዕሁፋዊ ተግባቦት እንዳይዳከም ተዘውትረው ጥቅም ላይ የሚውሉ የቋንቋው መዋቅራዊ ቅርፆችና ቃላት ላይ ትኩረት ማድረግን ይጠይቃል።

2.4.3. <u>ዘላቂነት</u> ፣ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ተማሪው ከክፍል ውጪም ሊለማመድባቸው የሚያስችሉት መሆን አለባቸው። ይህም ይዘቶቹ ለረዥም ጊዜ ሊያገለግሉ መቻላቸው ዘላቂነትን እንደሚያሳይ ያስገነዝባል። በጽህፈት ትምህርት የስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም ዘላቂነት ላለው ይዘት እንደምሳሌ ሊጠቀስ ይቻላል። ስርዓተ ነጥቦች ቋሚነት

ያላቸውና የጽሁፍ ውስጥ የተለያየ ግልጋሎት የሚሰጡ ምልክቶች ናቸው ( Harriss 1993 Pincas 1982) ::

2.4.4. አስደሳችነት፣ ተማሪው የሚቀርቡለት ይዘቶች በአካባቢው የሚያገኛቸውና ለሕይወትም ቅርበት ያላቸው ከሆኑበት ሊያስደስቱት ይችላሉ ። በአንፃሩም ከገጠመቱ የራቁ ከሆኑ ግራ የሚያጋቡት ይሆናሉ። የይዘቶች አስደሳችነት ከተተግባሪነት ጋርም ተያያዥ መሆን አለበት። በጽህፈት ክሂል የደብዳቤ አፃፃፍን ሲለማመድ የብዕር ጓደኛ አፍርቶ ሐሳብ የመለዋወጥ ዕድል ካገኘ የመግባባት አቅሙ ይጎለብታል። በውጤቱም እየረካበትና እየተበረታታ ይሄዳል። ተማሪው ሊሞክረው የሚችለው ይዘት ስለሚያስደስተው እርካታን ያስገኝለታል። ስለዚህ አስደሳችነት የተማሪውን ትግር በማቃለልና እቅዱንም በማሟላት ስሜቱን የሚስበውን በመምረጥ ላይ የተመሠረተ መስፈርት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል (cunnings worth 1983 Tyler 1949)።

2.4.5 ለመማር ያላቸው አመቺነት ፣ (learnabity), የትምህርት ይዘቶች ሲመረጡ የቀደሙትን መሠረት ማድረግ ይገባቸዋል። ይህም ትምህርቱን ለተማሪው ትርጉም አዘል ያደርግለታል። ከፊደላት ቅርፅ መለየት በኋላ የቃላት አመሠራረት ከዚያም የዓረፍተ ነገር አወቃቀር እያለ የሚያስጉዝ ይዘት ለመማር አመቺነት ያለው ነው።

ከላይ ለማሳየት የተሞከሩት የይዘት መምረጫ መስፈርቶች አንዱ ለአንዱ ድጋፍ የሚሰጡ ናቸው። ምክንያቱም በዓላማው የታሰበው የባህርይ ለውጥ የሚገኘው በሁሉም መጣመር ስለሆነ ነው። በነዚህ መስፈርቶች የተመረጡ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ዓላማን ከግብ ለማድረስ እንዴት ተደራጅተው መቅረብ አለባቸው? ለሚለው ጥያቄ ደግሞ ከዚህ ቀጥሎ መልስ ለመስጠት ይሞከራል።

2.5 <u>የጽህፈት ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት</u> ፣ የይዘት አደረጃጀት የተወሰኑ መስፈርቶችን መሰረት አድርገው የተመረጡ ይዘቶች በውል የሚያያዙበት ስልት ነው። በሌላ አገላለፅም ይዘቶችን ለትምህርት አቀባበል ምቹ አድርጎ ማቀናበር ነው። Ponser እና Rudensky ( 1986-90) " ይዘቶችን ማደራጀት ማለት እንደ ባዶ አጥንት የሚቆጠረውን የትምህርት ዓላማ ሥጋ ማልበስ ነው።" ይላሉ። በዚህም ይዘቶችን ማደራጀት በይዘቶች መካከል መተጋገዝና ህብረት መፍጠር መሆኑን መረዳት ይቻላል።

የጽህፈት ክሂል ይዘቶች የቋንቋውን ስርዓትና አጠቃቀም ድርና ማግ አድርገው አንዱ ለሌላው ድጋፍ እየሆኑ ይደራጃሉ። የቋንቋ ትምህርት ይዘት ምርጫና ቅንብርን አጣምሮ ይይዛል። ምርጫ ምን ይቅረብ ሲል ቅንብር ደግሞ በምን ቅደም ተከተል ይቅረብ ለዚህስ መመዘኛው ምንድነው ይላል። በዚህ መሠረት እያንዳንዱ ይዘት የቀደመውን መሠረት በማድረግ መደራጀቱ ዋና ጉዳይ መሆኑን ማጤን ይቻላል።

የትምህርት ይዘቶችን ማደራጀት ከሰው ልጅ የማወቅ ባህርያት አኳያ ተጠየቃዊና ስነልቡናዊ በሆነ ቅደም ተከተል በደረጃ ማስቀመጥ ነው ( Taba 1962 Bloom 1956 Tyler 1949) ።

ይዘቶቹን ለማደራጀት መርሆች ሆነው የሚያገለግሉት ተዋረዳዊና ጎናዊ አደረጃጀት በመባል ይጠራሉ (Cunnungs woth 1995 Reid 1993 Nunan 1992 Yalden 1987 Corder 1973 Tyler 1949)።

2.5.1 <u>ተዋረዳዊ አደረጃጀት</u> ፣ (Vertical Organilation) ይህ የአደረጃጀት መርህ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች በጊዜ ሂደት ውስጥ የሚኖራችው ዕድገት ተዛምዶ የሚገልፅበት ነው። ስለዚህም አዳዲስ የቋንቋውን አካላት የአቀራረብ አድማስ ለመወሰንከተማሪው

አንባር ስነትምህርታዊና ስነልሳናዊ ግምት መጨበጥ አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም ሰዎች መማር የሚችሉት እንዴት እንደሆነ ማወቅም ለአደረጃጀት የሚረዳ ነጥብ ነው። ሰዎች ሊማሩ የሚችሉት ከቀደመው ዕውቀታቸው ጋር ሊዛመድ በሚችል ይዘት አማካይነት ነው (Brown 1982 Bloom 1956) ።

የመማሪያ መፃህፍት አዘጋጆች የትኛው ለየትኛው መሠረቱ ነው? የሚለውን ጥያቄ ቀድመው መመለስ አለባቸው ። Tyler ( 1949 : 83) " አንድ ይዘት ብቻውን በአንዱት ጀምበር ጠቃሚ የሆነ የባህርይ ለውጥ አያስገኝም።" በማለት ዓላማን ለማሳካት የትምህርት ይዘቶች በጊዜ ብዛት እየተካካቡ መቅረብ እንዳለባቸው ያስረዳሉ።

በተዋረዳዊ አደረጃጀት ስር የሚመደቡት የተለያዩ መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው።

2.5.1.1. <u>ተከታታይነት</u> Ξ(Continuty) ይህ መስፈርት አንድን ክሂል የሚያጎለብቱ ጠቃሚ ነጥቦች ተደጋግሞ መምጣትን ያመለክታል። ተማሪው ከአንድ የቋንቋ ትምህርት ይዘት ጋር አንድ ጊዜ በመተዋወቁ ብቻ የተፈለገውን የባህርይ ለውጥ ስለማያመጣ ሊደጋገምለት ይገባል። ተከታታይነት ተማሪው የትምህርት ይዘቶችን እንዳይረሳው የሚያግዘው መስፈርት ነው። እዚህ ላይ የትኞቹ ይዘቶች መደጋገም እንደሚገባቸው መለየት ሌላው ተግባር መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። ድግግሞሹ ብቻ እንዲታወሱ ሊያደርጋቸው ስለማይችል በተማሪው የዕለት ተዕለት ሕይወቱ በተግባር በሚያውላቸው ይዘቶች ላይ ማተኮር ያስፈልጋል። ለጽህፈት ክሂል የተከታታይነት መስፈርት የደብዳቤ አፃፃፍ ከዝቅተኛ ክፍል ጀምሮ እየተደጋገመ የቀረበ ይዘት መሆኑ በምሳሌነት ሊጠቀስ ይችላል። ደብዳቤ በግላዊም ሆነ በማህበራዊ ህይወት የሚኖረው ድርሻ ቀላል አለመሆኑን ከግምት ውስጥ ያስገባ አደረጃጀት ነው ማለት ይቻላል።

2.5.1.2. <u>ተለጣጣቂነ</u>ት፤ (Sequence) የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ ከዓላማው ጋር እንዲስምሩ ተደርገው ተጠያቂዊ በሆነ መልክ በቅደም ተከተል የሚቀርቡበት ስልት ነው። በየክፍል ደረጃው ሊኖራቸው የሚገባውን የመነሻና የመድረሻ ነጥብ በመያዝ የሚገጣጠሙበት ነው። በዚህም ከቀላል ወደ ከባድ፤ ከነጠላ ወደ ውስብስብ፤ ከቅርብ ወደ ሩቅ ተጠያቃዊ አካሄድን ተከትሎ የሚደራጅበት መስፈርት ነው። ተማሪው የቱን መቼ መማር እንዳለበት ካወቅን ይህም ለምን እንደሚሆን ቀድመን ከተረዳን የተለጣጣቂነትን ጥያቄ መመለስ መቻላችን ነው።

በስነልቡና ምሁራን አገላለፅ መማር ማለት አዲሱን ዕውቀት ከቀደመው ጋር ማዛመድ መቻል መሆኑን በቀደመው የጽሁፍ ክፍል ለማሳየት ተሞክሯል። በዚህም መሠረት የጽህፈት ክሂል ይዘቶችም ለመማር ይችሉ ዘንድ ከቀላል ወደ ከባድ እየተሰናሰሉ ሊደራጁ ይገባቸዋል። Reid ( 1993፣86) " በፅህፈት ክሂል ረገድ ከቃላት ወደ ሐረጋት ከዚያም ወደ ዓረፍተ ነገሮችና አንቀፆች ምስረታ በደረጃ መሸጋገር የተለጣጣቂነትን መስፈርት የሚያሳይ አደረጃጀት ነው።" ይላሉ። ስለዚህ ልጥጥቅ የሰመረ እንዲሆን ይዘቶች ከተማሪው የአስተሳሰብና የግንዛቤ ደረጃ ጋር ተጣጥመው መቅረብ ይገባቸዋል ማለት ነው። የትምህርት ይዘቶች ከሰው ልጅ የማወቅ ባህርያት በተለይም ከግንዛቤ ባህርይ (Cognitive domain) አኳያ በዕድገት ተከታታይነታቸው ተከፍፋለው መቅረብ አለባቸው። በዚህም መሠረት ይዘቶች ዕውቀት ሽግግር ተግባቦትና - ትችት በሚል ቅደም ተከተል ይከፈላሉ ( Vallette & Rence 1972 Taba 1962 Bloom 1956) ።

በነዚህ ምሁራን የአከፋፈል ስልት መሠረት የትምህርት ይዘቶች ከቀየባህርይ ለውጥ ወደ ውስብስብ የባህርይ ለውጥ ሊያሸጋግሩ የሚችሉ መሆን አለባቸው። አከፋፈሉም የሚከተሉትን የትምህርት ክፍሎች ይይዛል።

ዕውቀት ፣ Knowledge) ማስታወስንና መገንዘብን የሚጠይቅ

የአንድ ክሂል ዝቅተኛው የትምህርት ደረጃ ነው።

ምሳለ ፣'የአንቀፅ ምንነትና አወቃቀርኙ መለየት

ሽግግር ፣ (Trasfer) ዕውቀትን ተርጉሞ በስራ ላይ የማዋልን

ሁኔታ የሚይዝ የትምህርት ክፍል ነው።

ምሳሌ ፣ ' የተዘበራረቁ ዐረፍተ ነገሮችን

በማስተካከል አንቀፅ ማደራጀት'

ተግባቦት ፣(Communication) ተረድቶ የመግለፅንና የትግበራን ችሎታ

የሚያሳይ የትምህርት ክፍል ነው።

ምሳሌ ፣ በአንድ አንቀፅ ሐሳብን መግለፅ

ትችት ፣ (Criticism) ሂሳዊ አመለካከትንና አስተያየት አዘል የሐሳብ

አቀራረብን የሚጠይቅ የክሂል ከፍተኛው የትምህርት ደረጃ ነው። በዚህም

እውነታን ከመላምት፣ ልዩነትን ከአንድነት ፤ ተገቢን ከኢተገቢ በመለየት

የመፍረድን ሁኔታ ያካትታል።

ምሳሌ ' አንቀፅን ማሳጠር'

በነዚህ የትምህርት ክፍሎች የሚመደቡት ይዘቶች የትኛው ለየትኛው መሠረት እየሆነ ከቀላል ወደ ከባድ መደራጀታቸውን መረዳት የሚያዳግት አይሆንም። እነዚህ የትምህርት ክፍሎች ለተለጣጣቂነት አደረጃጀት በእጅጉ የሚረዱ ናቸው።

በተጨማሪም በተዋረዳዊ አደረጃጀት ውስጥ ምጣኔንና ድረጃን መመልከት ያስፈልጋል። ምጣኔ የትምህርት ይዘቶቹን ከተማሪው ችሎታ አኳያ የመመጠን ሁኔታ

የሚጠይቅ ሲሆን ይህም ለትምህርቱ የተመደበውን ጊዜ ከግምት ውስጥ ማስገባትን የሚፈልግ ተግባር ነው። ድረጃ በየክፍለ ትምህርቱ ምን ያህል ይዘቶች ይካተቱ ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚያስገኝ አደረጃጀት ነው። የትምህርት ይዘቶቹን ሚዛናዊነት በተማሪው ደረጃ መጠበቂያ ስልት ነው።

ተዋረዳዊ አደረጃጀትን ከተከታዩ ንድፍ የበለጠ መረዳት ይቻላል። የቀስቶቹ አካሄድ የየክሂሉ ይዘቶች በየክፍል ደረጃው በጊዜ ብዛት እየቀጠሉ የሚጓዙ መሆኑን ነው።

| የክፍል ደረጃ | ማዳመጥ | መናገር | ማንበብ | መፃፍ |
|---|---|---|---|---|
| ስምንተኛ | ↑ | ↑ | ↑ | ↑ |
| ሰባተኛ | │ | │ | │ | │ |
| ስድስተኛ | │ | │ | │ | │ |
| አምስተኛ | │ | │ | │ | │ |

* የክሂሎችን ተዋረዳዊ አደረጃጀት ለመማልከት Reid ( 1993:81) ላይ ያቀረቡትን መሠረት በማድረግ ለጥናቱ እንደሚስማማ ተደርጎ የተዘጋጀ መግለጫ

<u>ጎናዊ አደረጃጀት</u> ፣ (Horizontal Organiation) በትምህርት ይዘቶች መካከል መኖር የሚገባውን ዝምድና የሚመለከት የአደረጃጀት መርህ ነው። የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ከሌሎች ክሂሎች ጋር ያለው ጥምረት የሚታይበትም ነው። Cunningsworth (1995 : 15) "የክሂሎችጥምረት ለአጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። እንዲዚያውም እንደ አምስተኛው ክሂል ሊቆጠር ይገባዋል "፡፡ ይላሉ። ከዚህም ለመረዳት የሚቻለው ከይዘቶች ጎናዊ አደረጃጀት የሚገኘውን እርባና ነው። በዚህም መሠረት የማስታወሻ

አያያዝ፤ የቃለ መጠይቅ ዝግጅትና የቃል ጽህፈት ሁሉንም ክሂሎች አጣምረው የሚይዙ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች መሆናቸውን መጠቆም ይቻላል።

የቋንቋ ብቃት የሚገኘው ለረዥም ጊዜ በሚደረግ በተጣመረና ትርጉማዊ በሆነ የክሂሎች ልምምድ ነው። በዚህም እያንዳንዱ ክሂል በጋራና በተናጠል ሊዳብር ይችላል (Yalden 1987 Tyler 1949) ።

በሌላ በኩል ቋንቋ የትምህርት መሠረት በመሆኑ ለተለያዩ ፅንሰሐሳቦች መግለጫነት መብቃት አለበት ። ፣ ስለዚህ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር ተዋህደው ሊደራጁ ይገባል። መሠረታዊ የቁጥር ትምህርት ይዘቶችን ከሌሎች የትምህርት ዓይነት ይዘቶች ጋር ማዛመድ አንዱ የውህደት ገፅታ ነው። የቋንቋን ትምህርት ይዘትም ከሌላ ትምህርት ይዘት ጋር ማዛመድ በራሱ አንድ የትምህርት ይዘት ማግኛ መንገድ ነው (Yalden 1987 Tyler 1949) ። ይህ ሁኔታ የሚያመለክተው ደግሞ በትምህርት ይዘቶች መካከል መደጋገፍ ያለ መሆኑን ነው። ይህም የተማረው እውቀት እንዲዳብርና የሚረዳ ለሁለንተናዊ ስብዕናውም የሚበጀው አካሄድ መሆኑን ያስገነዝባል።

የጽህፈት ክሂል ይዘቶችም ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር ተዋህደው እንዲቀርቡ የማድረግ አስፈላጊነቱ የሚያጠያይቅ አይደለም Carrol እና Willson ( 1993 : 260) " ከአንቀፅ አፃፃፍ ዓይነቶች አንዱ የሆነው አንድን መንደርደሪያ በተለያዩ አንቀፆች ውስጥ ማስገባት ነው። ይህም ለታሪክና ለጂኦግራፊ ትምህርቶች የሚመረጥ የአፃፃፍ ስልት ነው" ይላሉ። ከዚህም ለመረዳት የሚቻለው የአንቀፅ አፃፃፍ ከሌሎች ጽንሰሐሳቦች ጋር በመጣመር ሊያስገኝ የሚችለውን የውህደት ጠቀሜታ ነው።

ኅናዊ ቅንብር በአንድ የክፍል ደረጃ የሚገኙ የተለያዩ የትምህርት ዘርፎች አንዱ ሊላውን ለማኅልበት የሚጫወተውን ሚና የሚያሳይ የአደረጃጀት መስፈርት መሆኑን ማጤን ይቻላል። ተማሪውን በእግረመንገድ ከሌሎች የዕውቀት ዘርፎች ጋር ያስተዋውቀዋል። የህግ እውቀት ያለው ሰው የማመልከቻ አፃፃፍ ህግጋትን ሊያጠና ይገባዋል። ይህም ከጽህፈት ክሂል ይዘት የሚገኘው ጠቀሜታው ነው። ኅናዊ አደረጃጀቱ ህግንና ጽህፈትን በማጣመር የሚያቀርብ ይሆናል እንደማለት ነው።

በተከታዮቹ መግለጫዎች መሠረት የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ከሌሎች ክሂሎችና የተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ጋር የሚኖራችውን ውህደት ለማጤን እንሞክር፤

* ቀስቶቹ ጽህፈት ከሌሎቹ ክሂሎች ጋር ያላችውን ተጣማሪነት ለማሳየት የገቡ ናችው።

| የክፍልደረጃ | ጽህፈት | ንባብ | መናገር | ማዳመጥ |
|---|---|---|---|---|
| ስምንተኛ | → | → | → | → |
| ሰባተኛ | → | → | → | → |
| ስድስተኛ | → | → | → | → |
| አምስተኛ | → | → | → | → |

' የጽህፈትንና የሌሎችን ክሂሎች ጥምረት ለማሳየት Reid ( 1993 : 80)

ያቀረቡትን መሠረት በማድረግ ለጥናቱ በሚስማማ መልክ የተዘጋጀ መግለጫ'

ቀስቶቹ ጽህፈት ከሌሎቹ የትምህርት ዘርፎች ጋር የሚኖረውን ኅናዊ ዝምድና ለማመልከት የገቡ ናችው።

| የክፍል ደረጃ | ጽህፈት | ታሪክ | ጂኦግራፊ | ሳይንስ |
|---|---|---|---|---|
| ስምንተኛ | → | → | → | → |
| ሰባተኛ | → | → | → | → |
| ስድስተኛ | → | → | → | → |
| አምስተኛ | → | → | → | → |

Reid ( 1993 : 80-81) ያቀረቡትን መሠረት በማድረግ የጽህፈት ክሂል ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር የሚኖረውን ውህደት ለማመልከት በጥናቱ አትጣሚ የተዘጋጅ መግለጫ

ከላይ በዝርዝር ለማመልከት እንደተሞከረው በሁለቱ አበይት የአደረጃጀት መርሆች ሥር ተከታታይነት (Continuty) ተለጣጣቂነት (Sequnce) ምጣኔ(Grading) ድረጃና( Staging) ውህደት( Integration) እንደሚገኙ ነው።

የይዘቶች አደረጃጀት በተማሪዎች የትምህርት አቀባበልና በመማር ማስተማር ብቃት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል የትምህርት ጉዳይ በመሆኑ የመስኩ ምሁራን የትኩረት ነጥብ ከሆነ ውሎ አድሯል (Tyler 1949 Corder 1973 Cunnings worth 1995) ። ስለዚህ የአደረጃጀት መስፈርቶችን ባህርያት ጠንቅቀው በማወቅ የመማሪያ መጻህፍት አዘጋጆች በአግባቡ በስራ ላይ ሊያውሏቸው ይገባል።

ከላይ በዝርዝር በተጠቀሙት ጥናቶችና ስራዎች መሠረት በዚህ ጥናት በተለይ የጽህፈትን ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት በተመለከተ በሚረዱትና ተዛማጅነት ባላቸው በመመርኮዝ የጥናቱ ዘዴ በሚቀጥለው ምዕራፍ ይቀርባል።

# ምዕራፍ ሦስት

## የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት የተከተለው የይዘት ትንተና የምርምር ስልትን ነው። ከይዘት ትንተና የምርምር ተግባራት አንዱ ስለሚጠናው ጉዳይ ገላጭ መረጃ መስጠት ነው። በዚህም መሠረት ጥናቱ በአዲስ አበባ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ በተዘጋጁት የመጀመሪያ ደረጃ የሁለተኛው እርከን የአማርኛ መፃህፍት ላይ ያሉትን የጽህፈት ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት ከይዘት አደረጃጀት መርሆች አኳያ ገምግሟል።

በቅድሚያ የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ ከተነደፉበት ዓላማ አኳያ ተለይተው ከጽህፈት ትምህርት ባህርያትና የይዘት አደረጃጀት መርሆች አኳያ ትንታኔ ቀርቦባቸዋል። በተጨማሪም በመጠይቆች የተገኙ መረጃዎች ማመሳከሪያ ሆነው ተተንትነዋል። በተለይም የተለጣጣቂነትን አደረጃጀት በተመለከተ በክለሳ ድርሳን የጽሁፍ ክፍል ለማሳየት እንደተሞከረው (Bloom 1956: Vallette እና Rence 1972) የትምህርት ይዘቶችን በዕድገት ተከታታይነታቸው ለመከፋፈል የተጠቀሙበት ስልት በስራ ላይ ውሏል። በነሱም አስተሳሰብ መሠረት ለአንድ ዓላማ ግብ ማስመቻትነት የሚመረጡ ይዘቶች የዕድገት ተከታታይነታቸውን ሊጠብቁ እንደሚገባቸው መገንዘብ ይቻላል። በዚህም መሠረት እውቀት - ሽግግር ተግባቦት ትችት እያለ በመሄድ የሚደራጅበት ስልት ነው። በዚህም ዕውቀት አነስተኛው፣ ትችት ደግሞ ከፍተኛው የትምህርት ክፍል መሆኑን እናያለን። ይዘቶች አንዱ ለአንድ መሠረት በመሆን ተለጣጥቀው የሚደራጅበት ጠቃሚ ስልት ነው። ስለዚህ የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹን ከዚህ አኳያ ለመገምገም ሙከራ ተደርጓል።

የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹን ከይዘት አደረጃጀት መርሆች አኳያ በመተንተንና ከመጠይቆች ከተገኙ መረጃዎች ጋር አቀናጅቶ በመገምገም ጥናቱ ይዟቸው ለተነሳው ጥያቄዎች መልስ ለመፈለግ ጥረት ተደርጎበታል።

ቀጥሎም የጥናቱ የመረጃ ምንጮች ፤ የናሙና አወሳሰድ ፤ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ፤ የመጠይቅና ቃለመጠይቅ አዘገጃጀት መግለጫ ይስጥባቸዋል።

3.1 <u>የመረጃ ምንጮች</u> ፤ በጥናቱ ዋነኛ የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለገሉት ከየክፍሉ መጻሕፍት ላይ የተወሰዱ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ናቸው።

ሌሎቹ የመረጃ ምንጮች ለጥናቱ በተመረጡት ክፍሎች /ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል/ በማገልገል ላይ ያሉ የአማርኛ መምህራን ናቸው ። ይህም የተደረገበት ምክንያት የጥናቱ ዓላማ ግቡን ሊመታ የሚችለው የቋንቋው መምህራን በክፍል ውስጥ በማስተማር ተግባር ላይ እያሉ በሚያስተውሏቸው ጉዳዮች ከሙያቸው አንፃር የሚሰነዝሩት ሐሳብ የይዘት አደረጃጀቱ ምን መልክ መያዝ እንዳለበት ሊጠቁም ስለሚችል ለጥናቱ አስተዋፅዖ እንዳለው በማመን ነው።

በተጨማሪም የመጻህፍቱ አዘጋጆች የመረጃ ምንጭ ሆነው እገዛ አድርገዋል። አዘጋጆቹን በጥናቱ ማካተት ያስፈለገበት ምክንያት ለተማሪው በእጁ የሚገባውን መጽሐፍ በማሰናዳት ረገድ የይዘት አደረጃጀት የሚጠይቃቸውን መሠረታዊ ጉዳዮች ያውቃሉ በሚል ግምት ነው። በዚህም ስለ ተማሪው ዳራዊ ዕውቀት ስለጽህፈት ክሂል ይዘቶች ምርጫና አደረጃጀት ያላቸው ግንዛቤ ለጥናቱ የሚኖረው አስተዋጽዖ ቀላል አይሆንም በሚል እምነት ነው።

3.2 <u>የናሙና አወሳሰድ ፣</u> ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ጥናቱ በሁለተኛው እርከን የአዲስ አበባ መስተዳድር ት/ቤቶች መገልገያ በሆኑት የአማርኛ መፃህፍት ላይ ያሉ የጽህፈት ክሂል ይዘቶችን የሚገመግም ነው።

ይህ ጥናት የአመቺነት ናሙና አመራረጥ ስልትን በመጠቀም ጥናቱን በመንግሥት ትምህርት ቤቶች ላይ አድርጓል። የዚህም ምክንያት ከመስተዳደሩ ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት ተማሪዎች የሚገኙት በመንግሥት ት/ቤቶች ስለሆነና የግልና የሚሲዮን ትምህርት ቤቶችም መረጃ ለመስጠት ባለመፍቀዳቸው ነው። በዚህም መሠረት በመስተዳድሩ ከሚገኙት ስልሳአራት የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ከየዞኑ ሁለት ሁለት ት/ቤቶችበዕጣ ተመርጠዋል። የትምህርት ቤቶቹም ዝርዝር ቀጥሎ የቀረበው ነው።

ከዞን አንድ ተስፋ ኮከብ ና ባልቻ አባነፍሶ

ከዞን ሁለት _አቡነ ባስልዮስ ናመቅደላ

ከዞን ሦስት ደጃዝማች ወንድራድ ናካራሎ

ከዞን አራት ዳግማዊ ምኒልክና ኮከበ ፅባህ

ከዞን አምስት ቀጨኔ ደብረሰላም ናኮልፌ

ከዞን ስድስት አቃቂና ቃሊቲ ናቸው።

በነዚህ ትምህርት ቤቶች ከ5ኛ - 8ኛ ክፍሎች አማርኛ በማስተማር ላይ ያሉ መምህራን መጠይቁን እንዲሞሉ ታስቦ መጠየቁ ከታደላቸው አርባ ስምንት መምህራን መካከል ሁለቱ መጠይቁን ሳይሞሉ በመመለሳቸው ከጥናቱ ውጭ ተደርገው በድምሩ የአርባ ስድስት ሰዎች ምላሾች ብቻ ተተንትነዋል።

ከመጻህፍቱ አዘጋጆች መካከል ፈቃደኛ ሆነው የተገኙት ስድስት ሰዎች የሰጡት መረጃም የጥናቱ አጋዥ በመሆን ትንታኔ ቀርቦበታል።

3.3 <u>የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች</u> ፣ በዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች በመሆን ያገለገሉት ይዘቶቹን መተንተንና ቃለመጠይቅ የጽሁፍ መጠይቅ ናቸው።

የምርምርን ዘዴን ፈርጀ ብዙ ማድረግ ምርምሩን አስተማማኝ ውጤትላይ ያደርሳል። መሣሪያዎቹ በሙሉግን ወደ ምርምሩ ጥያቄ ማነጣጠር እንደሚገባቸው ማሰብ ዋናው ጉዳይ ነው Brewery እና Hunter (1989) ። በዚህም መሠረት ከአንዱ የመረጃ መሰብሰቢ የጎደለውን ከሌላው በማሟላት ረገድ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን መጠቀም ለጥናቱ ያለውን እገዛና ጠቀሜታ መረዳት ይቻላል። ስለዚህ ሦስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በጥምር ሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል።

3.4 <u>የመጠይቆችና ቃለ መጠይቆች አዘገጃጀት</u> ፣ መጠይቆች ዝግና ክፍት በመባል የሚታወቁ ጥያቄዎችን እንደሚይዙ ይታወቃል። አብዛኛዎቹ ጥያቄዎች ዝግ ናቸው። የአንድ መጠይቅ ይዘት ፤ አቀራረፅ፤ አቀራረብና የጥያቄዎች ቀደም ተከተል መላሹን የማያስቸግረው ሆኖ ከተዘጋጀ የሚፈለገውን መረጃ የማስገኘት ብቃቱ ከፍተኛ ይሆናል (Susana 1996 Nachmias እና Nachmias 1987 Lang እና Heise 1975) ።

መጠይቆቹ ሲዘጋጁ በሙከራ ጥናቱ ላይ በተከሰቱ አንዳንድ ሁኔታዎች መሠረት አንዳንድ ጥያቄዎች ሊጨመሩ ሊቀነሱና ቅርፃቸውን ሊለውጡ ችለዋል። የጥያቄዎቹን ይዘትና አቀራረብ በተመለከተም በአንድ የስነልቡና መምህር በሁለት ከመጀመሪያ ዲግሪ በላይ ባላቸው መምህራንና በሦስት የድህረ ምረቃ (TEAM) ተማሪዎች አስተያየት

እንዲሰጥባችው ተደርገው በማሻሻያ ሐሳቡ መሠረት ተስተካክለው በስራ ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል።

መጠይቆቹም በሁለት ክፍል የተመደቡ ሲሆኑ በክፍል አንድ የመረጃ ሰጪዎቹን ዳራ ሁኔታ ለማወቅ የቀረቡ ጥያቄዎች ተካተዋል። በክፍል ሁለት የይዘት ምርጫንና አደረጃጀትን በተመለከተ ዘርዘር ያሉ ጥያቄዎች የያዙ ናችው።

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተናና የጥናቱ ውጤት

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በተለያዩ ዘዴዎች የተሰበሰቡት የጥናቱ መረጃዎች ተተንትነው ውጤቱ ይገለፃል። በቅድሚያም መረጃዎቹ በፈርጅ በፈርጅ ተለይተው በጥናቱ ሊመለሱ ከታሰቡት ጥያቄዎች አኳያ ትንታኔ ይቀርብባቸዋል። በስተመጨረሻም መረጃዎቹ ተገናዝበው የሚጠቁሙትን አቅጣጫ መሠረት በማድረግ የጥናቱ ውጤት ይቀርባል።

*4.1* *የመረጃ ትንተና ፤* ማንኛውም ምርምር ይዞት ለተነሳው ጥያቄ መልስ ለማስገኘት የሚደረግ ተጠየቃዊ ፍተሻ የመረጃ ትንተና ነው። በዚህም ለምርምር ተግባር የጀርባ አጥንት በመሆን እንደሚያገለግል ለመረዳት ይቻላል። የምርምርን ፈር ተከትሎ ከተሰራበትም አንድ ዓይነት ውጤት ላይ ያደርሳል ተብሎ ይታመናል። (Seliger እና Elena 1989 Brown 1988 Nachmias እና Naihmias 1987).

በዚህ ንዑስ ክፍል ከመማሪያ መጻህፍቱ ላይ በምልከታ የተገኙት የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ከየክፍሉ መምህራንና የመጻህፍቱ አዘጋጆች በመጠይቅ ከተገኙት መረጃዎች ጋር ተጣምረው ከይዘት አደረጃጀት መርሆች አኳያ ትንተና ይሰጥባቸዋል።

4.1.1. ከክፍል አንድ አጠቃላይ መረጃዎችን ለማግኘት ለመምህራን በቀረቡ ጥያቄዎች የተገኙ ምላሾች ትንተና

## ሰንጠረዥ 1

### ስለ መምህራኑ የተገኙ አጠቃላይ መረጃዎች መግለጫ

| የትምህርት | መላሾች | | የስልጠና ተቋም | መላሾች | | የትምህርት | መላሾች | | አማርኛን በማስተማር | መላሾች | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ደረጃ | በቁጥር | በመቶኛ | | በቁጥር | በመቶኛ | ዓይነት | በቁጥር | በመቶኛ | ያገልግሎት ዘመን | በቁጥር | በመቶኛ |
| 10+2 | 16 | 34.8 | አ.አ.ዩ | 7 | 15.2 | አማርኛ | 30 | 34.8 | 1-10 | 13 | 28.2 |
| 12+2 | 30 | 65.2 | ከ.መ.ት.ኮ | 17 | 37.0 | ሁለገብ | 16 | 65.2 | 11-30 | 33 | 71.8 |
| - | - | - | መ.ማ | 2 | 4.3 | | - | - | - | - | - |
| - | - | - | ባ.መ.ት.ኮ | 20 | 43.5 | - | - | - | - | - | - |
| ድምር | 46 | 100% | | 46 | 100% | | 46 | 100% | | 46 | 100% |

መጠይቁን ከሞሉት አርባ ስድስት መምህራን መካከል አብዛኞቹ መምህራን በዲፕሎማ ደረጃ በአማርኛ መምህርነት የሰለጠኑ ሆነው ተገኝተዋል። ይህም ስለቋንቋው ትምህርት በቂ ግንዛቤ ያስገኝላቸዋል የሚል ግምት አሳድሯል። አማርኛን በማስተማር ያላቸው የአገልግሎት ዘመንም የአብዛኞዎቹ ከ 11- 30 ዓመት ክልል ውስጥ የሚገኝ ነው። ይህ የማስተማር ልምድም ቋንቋውን በማስተማር ክንውን በተለይም የመማሪያ መጽሐፍትን ከመተግበር አኳያ አንዳንድ ሁኔታዎችን በመገንዘብ ገንቢ አስተያየት ለመሰንዘር ያስችላል ተብሎ ታምኗል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከመጻህፍቱ አዘጋጆች ጋር በተደረገ ቃለምልልስ አምስቱ በአማርኛ ቋንቋና ስነጽሁፍ የመጀመሪያ ዲግሪ አንዱ ደግሞ አማርኛን በማስተማር ስነዘዴ የማስተርስ ዲግሪ እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል። ለመጽሐፍ አዘጋጅነት ከሚጠየቁት መስፈርቶች ውስጥ ከአስር ዓመታት ያላነሰ የስራ ልምድና የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ከዚህ በላይ የትምህርት ደረጃ እንደሚገኙበት ከሥርዓተ ትምህርት ክፍል ለመገንዘብ ተችሏል። በአጠቃላይ የትምህርት ደረጃቸውና የስራ ልምዳቸው ስለቋንቋው ትምህርት ጥሩ ግንዛቤ ሊያስጨብጣቸው ይችላል የሚል ግምት አሳድሯል።

በተጨማሪም ከስድስቱ መረጃ ሰጪዎች መካከል ሁለቱ ብቻ የአንድ ሳምንት የመማሪያ መጻህፍት ዝግጅትን የተመለከተ ወርክሾፕ የተካፈሉ መሆናቸውንና የቀሩት አራቱ ምንም ስልጠና እንዳልተሰጣቸው ገልፀዋል። ከዚህም አብዛኞዎቹ አዘጋጆች በመርሐ ትምህርቱ ብቻ እየተመሩ የመሰላቸውን እንዳዘጋጁ ለመገመት አያዳግትም።

### 4.1.2 የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹን ምርጫና አደረጃጀት ለመለካት የተሰበሰቡ መረጃዎች፣

#### 4.1.2.1 የአምስተኛ ክፍል የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ዓላማን ከዳር ለማድረስ ያላቸውን ብቃት ለመለየት ከመጽሐፉ የተሰበሰቡ ይዘቶች ትንተና፤

የትምህርት ይዘቶች ዓላማን ከግብ ለማድረስ የሚያግዙ የመለማመጃ መሣሪያዎች እንደሆኑ ባለፈው ምዕራፍ ለመግለፅ ተሞክሯል። በዚህም መሠረት ይዘቶች ሲመረጡ በተማሪው አቅም ተመጥነው መሆን አለበት ተማሪው የቀደመ እውቀቱን ተጠቅሞ ሊሰራቸው የሚችላቸው ይዘቶች ተመርጠው ሊደራጁለት ይገባል ማለት ነው። ከተማሪው ችሎታ በላይ ሆነው ከትምህርት ልምዱና ገጠመኙ የራቁ ይዘቶችን መምረጥ የዓላማን ግብ መምታት በባዶ ላይ ማሰብ መሆኑን በርካታ የመስኩ ምሁራን ያምናሉ (Cunningsworth 1995 corder 1973 Bloom 1956 Tyler 1049) ::

ከላይ በተገለፀው መሠረት የአምስተኛ ክፍል ይዘቶች ከዓላማ ጋር ያላቸውን ትስስር በተመለከተ ዓላማን ከዳር ለማድረስ የሚያስችሉና የማያስችሉ ይዘቶች እንዳሉባቸው ለመገንዘብ ተችሏል። በዚህም መሠረት ለክፍሉ የጽህፈትን ክሂል ዓላማ ያሳካሉ ተብለው የቀረቡት ይዘቶች ከታች ያሉት ናቸው።

ቃላት - አገጣጥሞ ዓረፍተ ነገር መመስረት

ስርዓተ ነጥቦች- ሁሉንም ማለማመድ

ዓረፍተ ነገር- አገጣጥሞ አንቀፅ መፃፍ

መረጃ መሰብሰብ - ከቅርፃ ቅርፅ

ከፎቶግራፍ

ከግርጌ ማስታወሻ

ከካርታ

ከሰንጠረዥ

ከግራፍ

የደብዳቤ ቅርፅ - የላኪ አድራሻ

የተቀባይ አድራሻ

መግቢያ

ሐተታ

መዝጊያ

ተጠየቃዊ አስተሳሰብ -በቃል ወይም በጽሁፍ መግለፅ

የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ መስፈርቶች- የሕይወት ታሪክ መፃፍ

--ዜና ሕይወት መሰብሰብ

-ያነበቡትን በራስ ቋንቋ መግለፅ

ከመምህራን መምሪያ ላይ የተሰወረ

(ዝርዝሩን ከአባሪ 'ሐ' ይመልከቱ)

ከነዚህ ይዘቶች መካከል በአምስተኛ ክፍል ተማሪ ደረጃ ስለ ቃላት፤ ስርዓተ ነጥቦች ፤ የደብዳቤ ቅርጽ የቀረቡት ይዘቶች በመጠኑም ቢሆን ተማሪውን ሊያለማምዱት የሚችሉ ስለሆኑ ዓላማዎቹን የማሳካት መጠነኛ ብቃት ይታይባቸዋል። ምክንያቱም ተማሪው በመጀመሪያው እርከን ትምህርቱ የሚተኮርበት መሠረታዊ

ትምህርትን ማስጨበጥ እንደሆነ በአዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ጥራዝ (1985 :41)ላይ በግልፅ ተቀምጧል። በዚህም መሠረት ተማሪው በአንድ መምህር ብቻ እንዲማር ተደርጎ ወደ አምስተኛ ክፍል ይዛወራል። ስለሆነም ለዚህ ተማሪ የጽህፈት ክሂል ግብ መምታት ይዘቶቹ የሚያንሱ ሆነው አልተገኙም። በሌላ በኩል ደግሞ ስለ አንቀፅ ፤ መረጃ አሰባሰብ፤ ተጠየቃዊ አስተሳሰብና የሕይወት ቃሪክ አፃፃፍ የሚያወሱት ይዘቶች የተማሪውን ችሎታ የሚመጥኑ ሆነው አልተገኙም። ምክንያቱም አንቀፅን ለመመስረት ስለ ዋናና ዝርዝር ሐሳቦች ፤ ስለ ዓረፍተ ነገሮች የሐሳብ አንድነት፤ ግጥምጥምነትና ተጠየቃዊ ተለጣጣቂነት በቅድሚያ ሊገነዘብ ይገባዋል። ይህ ተግባር ደግሞ ሐሳብን በጽሁፍ የመግለፅ ችሎታን ይጠይቃል። ስለዚህ በዚህ ክፍል ተማሪው ተግባር ላይ ያውለዋል ብሎ ማሰብ ይከብዳል። የመረጃ አሰባሰብን በተመለከተም ያስተዋሉትን ነገር የግል አስተያየትን በማከል በጽሁፍ የማስፈርን ችሎታ ይፈልጋል። ተጠየቃዊ አስተሳሰብም ትችት አዘል ተግባር ነው። የህይወት ታሪክ አፃፃፍ ስሬ ንባብንና እየመረጡ በራስ ቋንቋ አቀናብሮ መፃፍን የሚፈልግ ተግባር ነው። እነዚህ ይዘቶች በዚህ ባህርያቸው ጠንከር ያሉ ሆነው ተገኝተዋል። ተማሪው ልምምድ ሊያደርግባቸው ካልቻለ ደግሞ ከዓላማው ጋር የሚስምሩ አይሆኑም የዓላማ ምሉዕ ብያኔ መያዝ ያለበት የባህርይ ለውጥን ብቻ ሳይሆን በተማሪው ሊሞከር የሚችለውንም ይዘት ነው። ስለዚህ ዓላማ የተሳካ እንዲሆን ይዘቶች ሲመረጡ በተማሪው ደረጃ በማየት ትኩረትና ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው። ( Bloom 1956 Tyler 1949)

ሰንጠረዥ 2

በክፍል ሁለት ይዘቶቹ የጽህፈት ክሂል ዓላማዎችን ከዳር ለማድረስ የሚያስችሉ መሆን አለመሆናቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ፤

ጥያቄ 1 የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ ዓላማን ከዳር ለማድረስ የሚያስችሉ ይመስልዎታል?

| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥ | በመቶኛ |
| ሀ | ያስችላሉ | 1 | 8.3 |
| ለ | በከፊል ያስችላሉ | 4 | 33.3 |
| ሐ | አያስችሉም | 7 | 58.4 |
| | ድምር | 12 | 100% |

ከላይ ለማየት እንደተሞከረው 1(8 3%) መላሾች ይዘቶቹ ዓላማዎቹን ከዳር ለማድረስ ያስችላሉ ሲሉ 4 (33.3%) መላሾች በመጠኑ ያስችላሉ ብለዋል። 7(58 4%) መላሾች ደግሞ አያስችሉም እንዳሉ ታውቋል። ከተጠያቂዎቹ አብዛኛውን ቁጥር የያዙት መላሾች ባመለከቱት መሠረት ይዘቶቹ ዓላማን ከግብ በማድረስ በኩል የብቃት ማነስ ችግር ይታይባቸዋል።

ሰንጠረዥ 3

ይዘቶቹ የጽህፈት ክሂል ዓላማዎችን ከዳር ለማድረስ የማያስችሉበትን ምክንያት ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ፤

ጥያቄ 2 በተራ ቁጥር አንድ መልስዎ አያስችሉም የሚል ከሆነ ምክንያቱ ከተከታዩቹ ምርጫዎች የትኛው ይመስልዎታል ?

| | | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | አብዛኛዎቹ ይዘቶች ለክፍሉ ደረጃ የማይመጥኑ በመሆናቸው | 9 | 81.8 |
| ለ | የይዘቶቹ ቅደም ተከተል የተዛባ በመሆኑ | 2 | 18.2 |
| ሐ | ሌላ መልስ ካለዎት ይግለፁ | - | - |
| | ድምር | 11 | 100% |

ይዘቶቹ ዓላማዎቹን ከዳር ለማድረስ የማያስችሉበት ምክንያት በ9 (81.8/ መላሾች የይዘቶቹ ለክፍሉ ደረጃ አለመመጠን ሆኖ ሲገለፅ በ2(18.2/ መላሾች ደግሞ የይዘቶቹ ቅደም ተከተል መዛባት መሆኑ ተጠቁሟል። በዚህም መሠረት መረጃው በዓላማና በይዘት መካከል ያለመጣጣም ችግር እንዳለ ፍንጭ የሚሰጥ ሆኖ ተገኝቷል።

አንዳንድ መምህራንም በሰጡት ተጨማሪ አስተያየት አብዛኛዎቹ የአምስተኛ ክፍል ይዘቶች ተማሪው ሊሰራቸው የማይችላቸው መሆኑን በተግባር ያረጋገጡት ስለሆነ ዓላማን የማሳካት ብቃት እንደሚያንሳቸው ገልፀዋል። ይህም የሚያመለክተው ይዘቶቹ ወደ ተነደፈው ዓላማ በማድረስ ረገድ ተማሪው ሊለማመድባቸው የሚያስችሉት ሆነው አለመመረጣቸውን ነው። ስለዚህ ይዘቶች ሲመረጡ ወደ ዓላማው መንገዝ የሚያስችሉ የቋንቋ

አካላት ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ ምሁራን ይመክራሉ ( Cunningsworth: 1995 Yalden: 1985 Corder :1973 Tyler 1949) ::

ከመጽሐፉ አዘጋጆች አንዱ ይዘቶቹ ዓላማውን የማሳካት ብቃታቸው መጠነኛ እንደሆነ ሲገልፁ አንደኛው ግን ተማሪው ሊሞክራቸው የማይችላቸው በርካታ ይዘቶች ስላሉበት ሙሉ በሙሉ ከዓላማ ጋር ይጣጣማሉ ለማለት እንደማይደፍሩ ጠቁመዋል። ከዚህም ምላሽ በዓላማና በይዘት መካከል የስምረት ችግር መኖሩን መገንዘብ ይቻላል።

4 1 2 2 የአምስተኛ ክፍል የጽህፈት ክሂል ይዘቶች የመምረጫ መስፈርቶችን የጠበቁ መሆን አለመሆናቸውን ለመለየት ከመጽሐፉ የተገኙ ይዘቶቹ ትንተና

የቋንቋን ክፍሎች በሙሉ በአንድ ጊዜ ለትምህርትነት ማቅረብ ስለማይቻል የተወሰኑትን መርጦ በተማሪው ደረጃ እየመጠኑ ማቅረብ የግድ ነው። ለብዙ ምሁራን የጋራ ሆነው የሚያገለግሉት የይዘት መምረጫ መስፈርቶችም ተገቢነት፣ አስፈላኒት፣ ዘላቂነት፣ አስደሳችነትና ለመማር ያላቸው አመቺነት ናቸው (Yalden 1987 Cunningsworth 1984 Taba 1962 Tyler 1949) ::

የይዘቶች ተገቢነት የሚታየው ተማሪው በተግባር ሊያውለው ከመቻሉ አኳያ ፣አስፈላኒት ተዘውትሮ ጥቅም ላይ ከመዋሉ አኳያ ፣ ዘላቂነት ለረዥም ጊዜ ሊያገለግል ከመቻሉ አኳያ ፣ አስደሳችነት በደረጃው ተጠቅሞበት በውጤቱ ከመበረታታት አኳያ ፣ ለመማር ያለው አመቺነት ደግሞ ከቀደመ እውቀቱ ጋር ለመዛመድ ከመቻሉ አኳያ ነው። በዚህ መሠረት ለዚህ ክፍል የተመረጡት የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ከመስፈርቶቹ አኳያ ሲታዩ ብቃታቸው አነስተኛ ሆኖ ተገኝቷል። ምክንያቱም ተማሪው ሊሠራቸው የሚችላቸው

ይዘቶች የተወሰኑ በመሆናቸው ነው። በዚህም መሠረት ቃላትን ፤ ስርዓተ ነጥቦችን፤ የደብዳቤን ቅርፅ የተመለከቱት ይዘቶች ተገቢ፤ አስፈላጊ፤ ዘላቂ፤ አስደሳችና ለመማር ያላቸው አመቺነት በመጠኑም ቢሆን የተጠበቁ ሆነው ተገኝተዋል። የቀሩት ይዘቶች ግን ለክፍሉ ተማሪ ካለመመጠናቸው የተነሳ በመስፈርቶቹ መሠረት የተመረጡ ናቸው ለማለት የሚያስደፍሩ አልሆኑም ።

( ለዝርዝሩ አባሪ 'ሐ' ይመልከቷል)

ሰንጠረዥ 4

ይዘቶቹ የመምረጫ መስፈርቶችን የጠበቁ መሆን አለመሆናቸውን ለመለየት ለመምህራኑ ለቀረበ ጥያቂ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

ጥያቄ 3 የይዘቶቹ አደረጃጀት መስፈርቶች ምን ያህል የተጠበቁ ናቸው ብለው ያምናሉ ?

| | | አማራጭ መልሶች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | | |
| | | መልሶች | | መልሶች | | መልሶች | | ድምር | |
| ተ.ቁ | የይዘት መምረጫ መስፈርቶች | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ተገቢነት | - | - | 4 | 33.4 | 8 | 66.6 | 12 | 100 |
| ለ | አስፈላጊነት | - | - | 7 | 58.3 | 5 | 41.7 | 12 | 100 |
| ሐ | ዘላቂነት | - | - | 8 | 66.6 | 4 | 33.4 | 12 | 100 |
| መ | አስደሳችነት | - | - | 3 | 25 | .9 | 75 | 12 | 100 |
| ሠ | ለመማር ያላቸው አመቺነት | - | - | 2 | 16.7 | 10 | 83.3 | 12 | 100 |
| ረ | ሌላ ካለ ይገለፅ | - | - | - | - | - | - | - | - |

የይዘቶቹን ምርጫ በተመለከተ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው 4 (33.4% )መላሾች ተገቢነታቸው መካከለኛ ነው ሲሉ 8(66. 6%) መላሾች ዝቅተኛው ነው ብለዋል።

አስፈላጊነትን በተመለከተ 7(58.3%) መላሾች መካከለኛ መሆኑን ሲያመለክቱ 5(41.7%) መላሾች ዝቅተኛ መሆኑን አመልክተዋል። በዘላቂነት አኳያ ደግሞ 8(66.6%) መላሾች መካከለኛ ነው ሲሉ 4(33.4) መላሾች ዝቅተኛ መሆኑን ገልፀዋል። 3(25%) መላሾች አስደሳችነቱ መካከለኛ ነው ሲሉ 9(75%) መላሾች ዝቅተኛ ነው ብለዋል። ለመማር ያላቸውን አመቺነት 2(16.7%) መላሾች መካከለኛ ነወ ሲሉ 10(83.3%) መላሾች ዝቅተኛ መሆኑን ጠቁመዋል። በዚህም መሠረት አብዛኛውን ቁጥር የያዙት መላሾች ተገቢነትን ፤ አስደሳችነትንና ለመማር ያላቸው አመቺነት በዝቅተኛ ደረጃ እንደሚገኝ ማመልከታቸው ታውቋል። ስለዚህ በነዚህ የመምረጫ መስፈርቶች አኳያ ችግሩ መኖሩን መገንዘብ ያስችላል። በሌላ በኩል ደግሞ ይዘቶቹ አስፈላጊና ዘላቂ መሆናቸው በአብዛኛው ተጠያቂዎች መካከለኛ መሆናቸው በመገለጹ በዚህ ረገድም መጠነኛ ችግር መኖሩን ለማስተዋል ተችሏል። በተጨማሪም ሁሉም ተጠያቂዎች የመምረጫ መስፈርቶቹ በሙሉ በከፍተኛ ደረጃ ላይ አለመገኘታቸውን አመልክተዋል።

ከመጽሐፉ አዘጋጆችም አንዱ ይዘቶቹ በመምረጫ መስፈርቶች ስለተመረጡ ብቃት ያላቸው መሆኑን ሲገልፅ ሌላው ተጠያቂ ደግሞ የአጋጣሚ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር መስፈርቶቹ የታሰበባቸው አለመሆናቸውን ጠቁመዋል።

( ለዝርዝሩ አባሪ ‘ለ’ ን ይመለከቷል)

የይዘት መምረጫ መስፈርቶቹን በተመለከተ ከመረጃዎቹ ለማየት እንደተቻለው በአግባቡ ስራ ላይ የዋሉ ሆነው አልተገኙም። ስለዚህ በመስፈርቶቹ አጠቃቀም ረገድ ችግሩ ጎላ ብሎ የሚታይ ሆኗል።

4.1.2.3. የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹን የአደረጃጀት ብቃት ለመለየት ከመጽሐፉ የተገኙ ይዘቶች ትንተና

የትምህርት ይዘቶች በመምረጫ መስፈርቶች አማካይነት ቢመረጡም አንድ ዓይነት ውል ይዘው ካልተደራጁ የታለመውን የባህርይ ለውጥ ሊያስገኙ አይችሉም። ስለሆነም የአደረጃጀት መርህን ተከትለው ሊደራጁ ይገባቸዋል። በዚህም መሠረት የአምስተኛ ክፍል የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ከተከታታይነት ፤ ከተለጣጣቂነትና ከውህደት መርህ አኳያ ሲታዩ የሚከተለውን ይመስላሉ።

ከጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ ውስጥ ስለቃላት ፤ ዓረፍተ ነገር ምስረታና ስርዓተ ነጥቦች የቀረቡት ይዘቶች ተደጋግመው ታይተዋል። ይህም ከተከታታይነት መርህ አኳያ ሲታይ በጎ ጎን ሆኖ ተገኝቷል። ምክንያቱም ያለ ቃላት ዕውቀትና ያለ ዓረፍተነገር የሚከናወን የጽህፈት ሥራ ባለመኖሩ የይዘቶቹን ጠቃሚነት በማጤን የተደጋገመ አስመስሎታልና ነው። ይዘቶች አንድ ጊዜ ብቻ በመቅረባቸው ቋሚ ሊሆኑ ስለማይችሉ ተደጋግመው ሊቀርቡ ይገባቸዋል (Taba 1962 Tyler 1949) ።

በተለጣጣቂነት አኳያ ስንመለከት ደግሞ ከቀላል ወደ ከባድና ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ የመደራጀትን መርህ ተከትለው የቀረቡ ሆነው አልተገኙም። በዚህም ከዓረፍተ ነገር ምስረታ ወደ አንቀፅ ተሻግሮ የታያል። ስለተለያዩ ዓረፍተነገሮች ምስረታ ያወቀው ብቻ አንቀፅ ለመመስረት የሚያበቃው አይሆንም። ስለዚህ መቅደም የሚገባቸው ስለ አንቀፅ ምንነትና ባህርያት ሊያለማምዱ የሚችሉ ይዘቶች ነበሩ። በተለይ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎች በቅድሚያ ዕውቀት የሚያስጨብጡአቸው ይዘቶች ሊቀርቡላቸው ይገባል። ተለጣጣቂነት ተማሪው በአንድ ደረጃ ላይ ያገኘው ማጠቃለያ በሚቀጥለው ደረጃ ለመጠቀም ወደሚያስችለው እርከን ከፍ የማለቱን ጉዳይ

ያሳያል። የቀሩት ይዘቶችም ይህን የተከተሉ ባለመሆናቸው ከተማሪው ደረጃ በላይ ስለሆኑ ተለጣጣቂነታቸውን ጠብቀው የተደራጁ ባለመሆናቸውና ለችግሩ መኖር ጠቋሚ ናቸው።

የውህደትን አደረጃጀት በተመለከተ ስለመረጃ አሰባሰብ፤ ተጠያቃዊ አስተሳሰብና የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ የቀረቡት ይዘቶች የጽህፈትን ክሂል ከሌሎች ይዘቶችና የትምህርት ዘርፎች ጋር አጣምረው የያዙ ናቸው። የይዘቶቹ ባህርይ ሁሉንም ክሂሎች ስለሚያለማምዱና በእግረ መንገድም ከሌሎች የዕውቀት ዘርፎች ጋር ስለሚያስተዋውቁ በውህደት መርህ የተደራጁ ሆነው ተገኝተዋል። ውህደት የዕውቀትን አንድነት መፍጠሪያ በመሆን የሚያገለግል የአደረጃጀት መርህ ነውና (Taba 1962) ስለዚህም በውህደት አኳያ ያለው አደረጃጀት የጎላ ችግር አልታየበትም።

ሰንጠረዥ 5

የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹን የአደረጃጀት ብቃት ለመለየት ለመምህራኑ ለቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ፤

ጥያቄ 4 የይዘቶቹ አደረጃጀት መስፈርቶች ምን ያህል የተጠበቁ ናቸው ብለው ያምናሉ?

| | | አማራጭ መልሾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | | |
| | | መላሾች | | መላሾች | | መላሾች | | ድምር | |
| ተ.ቁ | የአደረጃጀት መስፈርቶች | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ተከታታይነት | 5 | 41.7 | 7 | 58.3 | - | - | 12 | 100 |
| ለ | ተለጣጣቂነት | - | - | 3 | 25 | 9 | 75 | 12 | 100 |
| ሐ | ውህደት | 10 | 83.3 | 2 | 16.7 | - | - | 12 | 100 |

ስለ ይዘቶቹ አደረጃጀት በተገኘው መረጃ መሠረት 5(41.7%) መላሾች ተከታታይነቱ ከፍተኛ ነው ሲሉ 7 (58.3%) መላሾች ደግሞ መካከለኛ መሆኑን ጠቁመዋል። አብዛኛዎቹ መላሾች መካከለኛ መሆኑን ስላመለከቱ በተከታታይነቱ አኳያ አሳሳቢ የሆነ ችግር አለመኖሩ ተገምቷል።

ተለጣጣቂነት በተመለከተ ደግሞ 3(25%) መላሾች መካከለኛ መሆኑን ሲያመለክቱ 9(75%) መላሾች ዝቅተኛ እንደሆነ ገልፀዋል። ከመላሾቹ አብዛኛዎቹ በተለጣጣቂነቱ ላይ ችግር እንዳለ የሚጠቁሙ ሆነው ተገኝተዋል።

አንዳንድ መምህራን በሰጡት ተጨማሪ አስተያየትም ስለተለጣጣቂነት ሲገልፁ የመጽሐፉ ዝግጅት የተማሪውን ችሎታ ያላጤነ ከመሆኑ የተነሳ ችግር ያለበት መሆኑን ጠቁመዋል። የተማሪውን ችሎታ ማነስ በተመለከተም በመጀመሪያው እርከን በአንድ መምህር ብቻ ትምህርቶቹ ሁሉ መስጠታቸውና ያለምዘና ወደ አምስተኛ ክፍል እንዲያልፉ መደረጋቸው ችግሩን እንዳባባሰው ጠቁመዋል። አንድ ተጠያቂም የፊደላትን ቅርፅ በውል ለይቶ ላላወቀ ተማሪ የተለያዩ ውስብስብ ባህርያት ያሉትን የጽህፈት ክሂል ለደረጃው በማይመጥን ሁኔታ ማቅረብ የተለጣጣቂነትን ፅንሰሐሳብ አለመረዳት መሆኑን ጠቁመው ይህም በማስተማር ወቅት ችግር እንደፈጠረባቸው ገልፀዋል።

የመጽሐፉ አዘጋጆችም ተለጣጣቂነታቸው አለመጠበቁን አመልክተዋል። ለዚህም እንደምክንያት አድርገው ያቀረቡት

1 እንዲያዘጋጁ የተጠየቁት የአንደኛና የአምስተኛ ክፍል

መጻህፍትን በመሆኑ ስለ አራተኛው ክፍል ይዘት ምንም ውል ባለመጨበጣቸው መሆኑን

2 የትኩሳና የይድረስ ይድረስ መሆኑን

3 ከመርሐ ትምህርት አዘጋጆቹ ጋር ባለመጣጣማቸው እንደሆነ አብራርተዋል።

ከይዘቶቹ ትንተና ሆነ ከመጠይቆቹ በተገኙት መረጃዎች መሠረት የተለጣጣቂነት አደረጃጀት ችግር እንዳለበት ለመገንዘብ ተችሏል። ይዘቶቹ የታለመላቸውን የባህርይ ለውጥ ያስገኙ ዘንድ ዕውቀት -ሽግግር - ተግባቦትና -ትችት በሚል ደረጃ ተከፋፍለው ሊቀመጡ ይገባል( Taba 1962 Bloom 1956) ። እንደ ምሁራኑም ገለፃ የትምህርት ይዘቶች መነሻቸው የዕውቀት ዘርፍ መሆኑንና ከፍተኛው ደረጃ ደግሞ ትችት መሆን እንዳለበት ነው። በዕውቀት ደረጃ ተማሪው ግንዛቤ የሚጨብጥበት ሲሆን ሽግግር ዕውቀቱን ተርጉሞ በስራ ላይ የሚያውልበት ነው። ተግባቦት የተባለው የትምህርት ክፍል ደግሞ የራሱን አስተያየት በመጨመር ራሱን የሚገልፅበት ነው። በመጨረሻም በትችት የትምህርት ክፍል ሂስና አስተያየት አዘል ፍርድ የመስጠት ችሎታውን የሚጠቀምበት ይሆናል። ከዚህ አንፃር የዚህ ክፍል ይዘቶች ደረጃቸውን ጠብቀው ያልቀረቡ በመሆናቸው የተነሳ የተለጣጣቂነት ችግር እንዳለባቸው ለመገንዘብ ተችሏል።

የውህደትን መርህ በተመለከተ 10(83.3%) መላሾች መካከለኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ሲገልፁ 2(16.7%) መላሾች ደግሞ መካከለኛ ናቸው ብለዋል። ስለሆነም ይዘቶቹ በውህደት አኳያ ከተለጣጣቂነት በእጅጉ የተሻሉ ሆነው ታይተዋል።

የመጻህፍቱ አዘጋጆችም አንዱ ከሌሎች ክሂሎች ጋር ያላቸው መደጋገፍ ከፍተኛ መሆኑን ሲገልፁ አንደኛው ግን እንደማይደጋገፉና እንዲያውም ዝግጅቱ ክሂል ተኮር አለመሆኑን ጨምረው ተናግረዋል። እንግዲህ ይዘቶቹ ሲታዘዝ ሆነ በመጠይቆቹ በተገኘው መረጃ መሠረት በውህደት አኳያ የጠና ችግር አለመኖሩ ታይቷል። ሆኖም

ቃለመጠይቅ ከቀረበላቸው መላሾች አንዱ የውህደት መርህ አለመጠበቁን መግለፃቸው ወደፊት በዚህ መስክ ለሚደረግ ጥናት ፍንጭ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል መሆኑ በጥናቱ አቅራቢ ታምኖበታል።

ሰንጠረዥ 6

የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ የተማሪውን ደረጃ የሚመጥኑ መሆን አለመሆናቸውን ለመለየት ለመምህራኑ በቀረበ ጥያቄ የተገኘ ምላሽ መግለጫ፤

ጥያቄ 5 የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ የተማሪውን ደረጃ የሚመጥኑ ይመስልዎታል?

| | | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ይመጥኑታል | 2 | 16.7 |
| ለ | አይመጥኑትም | 10 | 83.3 |
| | ድምር | 12 | 100% |

መረጃውን ከሰጡት አስራሁለት መምህራን መካከል 2(16.7%) መላሾች የተማሪውን ደረጃ የሚመጥኑ ናቸው ሲሉ 10(83.3%) መላሾች ደግሞ እንደማይመጥኑት አመልክተዋል። በአብዛኞቹ መላሾች መሠረትም ይዘቶቹ የተማሪውን ደረጃ ባለመመጠን አኳያ ችግር እንዳለባቸው ለመገንዘብ ተችሏል።

ሰንጠረዥ 7

የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ ለተማሪው ደረጃ የማይመጥኑበትን ምክንያት ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

ጥያቄ 6 በተራ ቁጥር አምስት መልስዎ አይመጥኑትም ከሆነ ምክንያቱ ከተከታዩቹ የቱ ይመስልዎታል?

| | | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | የተማሪውን የቀደመ ችሎታ | 6 | 60% |
| ለ | ስላላገናዘበ | 2 | 20% |
| ሐ | የተማሪውን ፍላጎት ስላልያዙ | 1 | 10% |
| መ | የጽህፈት ባህርይ በመዘንጋቱ | 1 | 10% |
| ሠ | መጠኑ ብዙ በመሆኑ | | |
| | ሌላ መልስ ካለዎት ይግለፁ | - | - |
| | ድምር | 10 | 100% |

የጽህፈት ክሂሎች ለተማሪው ደረጃ አይመጥኑም ካሉት አሥር መላሾች መካከል 6(60%) መላሾች የተማሪውን የቀደመ ችሎታ ባለማገናዘባችው መሆኑን ፣ 2(20%) መላሾች የተማሪውን ፍላጎት ባለመያዛችው መሆኑን 1(10%) መላሾች የጽህፈት ባህርይ በመዘንጋቱ መሆኑንና 1(10%) መላሾች ደግሞ መጠኑ በመብዛቱ መሆኑን አመልክተዋል። በአብዛኛዎቹ ተጠያቂዎች መሠረት ይዘቶቹ የተማሪውን የቀደመ ችሎታ የማምት ውስጥ በማስገባት ረገድ ችግር እንዳለባችው የሚጠቁሙ ሆነው ተገኝ ተዋል።

ከሁለቱ የመጽሐፉ አዘጋጆች አንዱ የተማሪው ፍላጎት በቅጡ ስላልተጠና ደረጃቸውን በመመጠን በኩል ችግር ሊኖርበት እንደሚችል ሲገልጹ አንደኛው ደግሞ የተማሪውን ፍላጎትና ችሎታ በማገናዘብ የቀረበ መሆኑን አመልክተዋል። ከሁለቱ መላሾች የአንዱን ብቻ በአስተማማኝ መረጃነት ለመውሰድ አስቸጋሪ ቢሆንም የተማሪውን ደረጃ በመመጠን ረገድ ግን ችግር መኖሩን የሚጠቁሙ ናቸው ማለት ያስችላል።

በአጠቃላይ የአምስተኛ ክፍልን የጽህፈት ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት አስመልክቶ በይዘቶቹ ላይ በተደረገው ትንተና በመጠይቆች በተሰባሰቡ መረጃዎች መሠረት ይዘቶቹን በተማሪው ደረጃ በመመጠን ረገድ ችግር እንዳለባቸው ታይቷል። ይህ ችግርም ይዘቶቹ ከዓላማ ጋር እንደይጣጣሙ፤ የይዘት አመራረጡ ሚዛናዊነት የጎደለው እንዲሆንና የይዘት አደረጃጀቱም የተዛባ እንዲሆን ማድረጉን ለመመልከት አስችሏል።

4.1.2.4 የስድስተኛ ክፍል የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ዓላማን ከዳር ለማድረስ ያላቸውን ብቃት ለመለየት ከመጽሐፉ የተገኙ ይዘቶች ትንተና ፤

ይዘቶችና ዓላማዎች ሊኖራቸው የሚገባውን ትስስር ቀደም ባለው ምዕራፍ ለመግለፅ ተሞክሯል። በዚህም መሠረት የሚመረጡት ይዘቶች ዓላማን የማሳካት ብቃት እንዲኖራቸው ጥረት ማድረግ እንደሚገባ መረዳት ይቻላል። አለበለዚያ የሁለቱ መጣጣም ማጣት ‘ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ’ እንደማለት ያስቆጥራል።

በዓላማና በይዘት መካከል መጣጣም እንዲኖር ከተፈለገ ይዘቶቹ ሲመረጡ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል። በዚህም መሠረት ለስድስተኛ ክፍል ከተመረጡት የጽህፈት

ክሂል ይዘቶች መካከል ኅላማን ከዳር በማድረስ ረገድ ብቃት የሚታይባቸውና የማይታይባቸው እንዳሉባቸው ለመረዳት ተችሏል። ለክፍሉ የቀረቡት ይዘቶችም በአብዛኛው ተከታዮቹ ናቸው።

ቃላት - የተዘበራረቁትን ቃላት በስርዓት ማስቀመጥ

በቃላት ዓረፍተ ነገር መገንባት

ዓረፍተነገር- ቅደም ተከተል ማስተካከል

- አደረጃጀት
- መመስረት
- ማሳደግና ማስፋፋት
- አገጣጥሞ አንቀፅ መገንባት

አንቀፅ -በአንቀፅ ውስጥ ባዶ ቦታዎችን መሙላት

- አንቀፆችን ማገናኘት
- መንደርደሪያና ዝርዝር ሐሳብ
- አንቀፆችን በአንድ ዓረፍተነገር ማሳጠር

ስርዓተ ነጥቦች- ድርብ ሰረዝ

ነጠላ ሰረዝ፤ ድርብ ሰረዝ፤ ቃለአጋኖ፤ ትዕምርተ ስላቅ

ሪፖርት - የተገኘን ሐሳብ ሪፖርት ማቅረብ

- በደን መመናመን ላይ ሪፖርት ማቅረብ
- በመጠየቅ ወይም በማንበብ ስለ ላሊበላ አብያተ
- ክርስቲያናት ሪፖርት ማቅረብ
- ጠይቀውና አንበበው ስፋሬ ዘገባዎች ማቅረብ

ሪፖርት ማዘጋጀት የሚያስችሉ መልመጃዎች

የሕይወት ታሪክ - የራስ ታሪክ መፃፍ

የደብዳቤ አፃፃፍ - የብዕር ጓደኛ ደብዳቤ

-ከት/ቤት ወይም ከስራ ቢቀሩ በደብዳቤ መግለፅ

ጥናትና ምርምር ማድረግ

የእጅ ፅሑፈት

ማስታወሻ አያያዝ የፅለት ማስታወሻ መመዝገብ

ምኞት ፍላጎትና ዝንባሌን በጽሁፍ መግለፅ

ሐሳብን በቃልና በጽሁፍ መግለፅ

አጫጭር ጽሁፎችን መፃፍ

አስተዋጽኦ መንደፍ

ግጥም ወደ ስድ ንባብ መለወጥ

ግጥም መጻፍ

(ለዝርዝሩ አባሪ 'ሐ ' ን ይመልከቷል )

ከነዚህ ለጽህፈት ክሂል መለማመጃነት ከሚያገለግሉ ይዘቶች መካከልበተማሪው ደረጃ ሊሰሩ የሚችሉት በሙሉ ዓላማውን ከግብ ሊያደርሱ እንደሚችሉ ማስተዋል የሚቻል ነው። በዚህም መሠረት ስለ ቃላት ፤ ዓረፍተነገር፤ አንቀፅ፤ ስርዓተ ነጥቦች፤ የሕይወት ታሪክ፤ የደብዳቤ አፃፃፍ ፤ ምኞች ፍላጎትና ዝንባሌን በጽሁፍ መግለፅ፤ አጫጭር ጽሁፎችን መፃፍ የዚህን ክፍል ተማሪ የጽህፈት ክሂል ሊያዳብሩለት የሚችሉ ይዘቶች ሊባሉ ይችላሉ። ምክንያቱም በስድስተኛ ክፍል ተማሪ ደረጃ ሊሞከሩ የሚችሉ ይዘቶች በመሆናቸው ነው። ከይዘቶቹ መካከል ለተማሪው ሕይወትና ለአካባቢው ቅርበት ያላቸው ጉዳዮች ስለሚገኙበት በተግባር ሊውሉ ይችላሉ ማለት ነው።

አንዳንዶቹ ይዘቶች ደግሞ የተማሪውን ደረጃ የጠበቁ ሆነው አልተገኙም ሪፖርት ማቅረብ፤ የጥናትና ምርምር ፅሁፍ፤ ግጥም ወደ ስድ ንባብ መለወጥ ግጥም መፃፍና አንቀፅን በአንድ ዓረፍተነገር ማሳጠር የሚሉት ይዘቶች ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑ ናቸው። ምክንያቱም እነዚህ ይዘቶች የመለየትን የማመዛዘንንና የመተቸትን ችሎታ የሚጠይቁ በመሆናቸው ነው። ይዘቶቹ በከፍተኛው የትምህርት ክፍል የሚመደቡ በመሆናቸው ለተማሪው ስለሚከብዱት ዓላማን መተርጎሚያ ይሆናሉ። የሚል እምነት አላሳደረም እነዚህ ትችት አዘል ይዘቶች መቅረብ የሚገባቸው ለሁለተኛ ደረጃና ለኮሌጅ ተማሪዎች ነው (Taba 1962 Bloom 1956) ።

ስለዚህ ይዘቶቹን ተማሪዎቹ የማይሠሯቸው ከሆኑ ወደ ዓላማው በየት በኩል ይደረሳል? ከዚህም የዓላማዎቹና የይዘቶቹ ስምረት በተማሪው የመስራት አቅም መወሰኑ የተዘነጋ መሆኑን ለመገመት ይቻላል። ስለዚህ በዓላማና በይዘት መካከል ያለመጣጣም ችግር እንዳለ ከመረጃዎቹ ለማየት ተችሏል።

ሰንጠረዥ 8

በክፍል ሁለት ይዘቶቹ የጽህፈት ክሂል ዓላማዎችን ከዳር ለማድረስ የሚያስችሉ መሆን አለመሆናችውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

ጥያቄ 1 የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ ዓላማን ከዳር ለማድረስ የሚያስችሉ ይመስልዎታል ?

| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥ | በመቶኛ |
| ሀ | ያስችላሉ | - | - |
| ለ | በከፊል ያስችላሉ | 7 | 70% |
| ሐ | አያስችሉም | 3 | 30% |
| | ድምር | 10 | 100 |

ከላይ ለማየት እንደተሞከረው ከመላሾቹ መካከል 7(70%) ያህሉ ይዘቶቹ ዓላማዎቹን ከዳር ለማድረስ በከፊል እንደሚያስችሉ ሲገልፁ 3(30%) መላሾች ደግሞ አያስችሉም ብለዋል። መላሾቹ በሙሉ በዓላማውና በይዘቱ መካከል ያለመጣጣም ችግር መኖሩን ስለሚጠቁሙ የችግሩን መኖር መቀበል የግድ ይሆናል።

ሰንጠረዥ 9

ይዘቶቹ ዓላማዎቹን ከዳር ለማድረስ የሚያስችሉበትን ምክንያት ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

ጥያቄ 2 በተራ ቁ. አንድ መልስዎ አያስችሉም የሚል ከሆነ ምክንያቱ ከተከታዮቹ ምርጫዎች የትኛው ይመስልዎታል ?

| | | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | በቁጥ | በመቶኛ |
| ሀ | አብዛኛዎቹ ይዘቶች ለክፍሉ ደረጃ የማይመጥኑ በመሆናቸው | 9 | 90% |
| ለ | የይዘቶቹቅደም ተከተል የተዛባ በመሆኑ | 1 | 10% |
| ሐ | ሌላ መልስ ካለዎት ይግለፁ | - | - |
| | ድምር | 10 | 100 |

ከመረጃ ሰጪዎቹ ለመገንዘብ እንደተቻለው 9(90%) ያህሉ ይዘቶች ዓላማውን ከዳር ለማድረስ የማይችሉት አብዛኛዎቹ ለክፍሉ ደረጃ ባለመመጠናቸው መሆኑን ሲገልፁ 1(10%) ያህሉ ደግሞ የይዘቶቹ ቅደም ተከተል በመዛባቱ ነው ብለዋል። በአብዛኛዎቹ መላሾች መሠረት ይዘቶቹን ለክፍሉ ደረጃ በመመጠን ረገድ ችግር መኖሩንና ይህም የየዓላማና የይዘት መጣጣም ችግር ማስከተሉን ማጤን ተችሏል።

ከመጽሐፉ አዘጋጆች አንዱ ይዘቶቹ በሙሉ ተማሪውን በማለማማድ ዓላማውን የማሳካት ብቃት አላቸው ሲሉ አንደኛው ግን ብዙዎቹ ይዘቶች ከዓላማ ጋር ሊገናኙ የማይችሉ መሆናቸውን ለዚህም ምክንያቱ ከተማሪው ደረጃ በላይ የሆኑ ይዘቶች በመካተታቸው መሆኑን ጠቁመዋል።

ዓላማ በይዘቶች ተተግባሪነት የሚገኝ የአስተሳሰብ፤ የአሰራርና የባህርይ ለውጥ ነው። ስለዚህ በዓላማና በይዘት መካከል ጠንካራ ቁርኝት ሊኖር ይገባል። Bloom(1956)

በዚህም መሠረት የዚህ ክፍል ይዘቶችና ዓላማዎቹ በአብዛኛው የሚጣጣሙ ሆነው አለመገኘታቸውን ከመረጃዎቹ መረዳት ይቻላል፡፡

4.1.2.5 የስድስተኛ ክፍል የጽህፈት ክሂል ይዘቶች የመምረጫ መስፈርቶችን የጠበቁ መሆን አለመሆናቸውን ለመለየት ከመጽሐፉ የተገኙ ይዘቶች ትንተና

ይዘቶች ተመርጠው የሚቀርቡበት ምክንያት ለመማር አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር መሆኑን ቀደም ባለው ምዕራፍ ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡ ለአብዛኛዎቹ የመስኩ ምሁራን የጋራ የሆኑት የይዘት መምረጫ መስፈርቶች እንዳሉም ተገልጿል፡፡ በዚህም መሠረት የስድስተኛ ክፍል የጽህፈት ክሂል ይዘቶች እነዚህን መስፈርቶች መሠረት ማድረግ አለማድረጋቸውን ቀጥለን እንይ

ለክፍሉ ከቀረቡት ይዘቶች መካከል ስለ ቃላት ፤ ዓረፍተነገር፤ ስርዓተ ነጥቦች፤ አንቀፅ፤ የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ፣ የደብዳቤ አፃፃፍ፣ ምኞትና ፍላጎት ዝንባሌን በጽሁፍ መግለፅና አጫጭር ጽሁፎች መፃፍ በመጠኑም ቢሆን ተገቢነት፣አስፈላጊነት ፣ ዘላቂነት አስደሳችነትና ለመማር አመቺነት ያላቸው ይዘቶች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ምክንያቱም የክፍሉ ተማሪ ሊሞክራቸው የሚችላቸው ይዘቶች ስለያዙ ነው፡፡ ከእነዚህ ይዘቶች መካከል ለተማሪው የዕለት ተዕለት ሕይወት ቅርበት ያላቸውና ገጠመኙን ለመግለፅ የሚያስችሉ ስላሉባቸው የይዘት መምረጫ መስፈርቶችን ከሞላ ጎደል የያዙ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

የቀሩት ይዘቶች ግን በተማሪው ደረጃ ሊሞከሩ የማይቻሉ በመሆናቸው በመምረጫ መስፈርቶች መሠረት የቀረቡ ሆነው አልተገኙም፡፡ ስለዚህ የተማሪውን ዳራዊ የጽህፈት ችሎታ በማገናዘብና የመምረጫ መስፈርቶቹን ባግባቡ በመጠቀም ረገድ ችግር እንዳለ ለመገንዘብ ተችሏል

( ለዝርዝሩ አባሪ ‘ሐ’ን ይመለከቷል)

ሰንጠረዥ 10

የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ የመምረጫ መስፈርቶችን የጠበቁ መሆን አለመሆናቸውን ለመለየት ለመምህራኑ ለቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

ጥያቄ 3 የይዘቶቹ አደረጃጀት መስፈርቶች ምን ያህል የተጠበቁ ናቸው ብለው ያምናሉ? ( 3 ከፍተኛ 2 መካከለኛ 1 ዝቅተኛ )

| | | አማራጭ መልሾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | | |
| | | መላሾች | | መላሾች | | መላሾች | | ድምር | |
| ተ.ቁ | የይዘት መምረጫ መቴፈርቶች | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ተገቢነት | - | - | 3 | 30% | 7 | 70 | 10 | 100 |
| ለ | አስፈላጊነት | - | - | 5 | 50% | 5 | 50% | 10 | 100 |
| ሐ | ዘላቂነት | - | - | 3 | 30% | 7 | 70% | 10 | 100 |
| መ | አስደሳችነት | - | - | 2 | 20% | .8 | 80% | 10 | 100 |
| ሠ | ለመማር ያላቸው አመቺነት | - | - | 2 | 20% | 8 | 80% | 10 | 100 |
| ረ | ሌላ ካለ ይገለፅ | - | - | - | - | - | - | - | - |

መጠይቁን ከሞሉት መምህራን መካከል 3(30%) ያህሉ የይዘቶቹ ተገቢነትና ዘላቂነት በመካከለኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ሲገልፁ 7(70%) ያህሉ ደግሞ በዝቅተኛ ደረጃ እንደሚገኙ ጠቁመዋል። 2(20%) መላሾች የይዘቶቹ አስደሳችነትና ለመማር ያላቸው አመቺነት መካከለኛ ነው ሲሉ 89(80%) መላሾች ደግሞ ዝቅተኛ ነው ብለዋል። 5(50%) መላሾች አስፈላጊነቱ መካከለኛ ነው ሲሉ 5(50% ደግሞ ዝቅተኛ ነው ብለዋል። በመረጃው መሠረት አብዛኛዎቹ መላሾች የይዘቶቹ ተገቢነት ዘላቂነት ፤ አስደሳችነትና ለመማር ያላቸው አመቺነት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ መገንዘብ ያስችላል በዚህም የይዘት መምረጫ መስፈርቶቹን በመጠቀም አኳያ ችግር መኖሩ ተስተውሏል።

አስፈላጊነትን በተመለከተ ግን ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ያሉት መላሾች እኩል በመሆናቸው አንዱን በአስተማማኝ መረጃነት ለመቀበል ቢያስቸግርም የችግሩን መኖር ፍንጭ ሊሰጡ እንደሚችሉ መገመት አስችሏል።

ከመጽሐፉ አዘጋጆች አንዱ ይዘቶቹ በብዛት አስፈላጊና ተገቢ ሲሆኑ ለመማር አመቺነት እንደሌላቸው ገልፀዋል። አንደኛው ደግሞ የይዘት መምረጫ መስፈርቶቹ በሙሉ በአጥጋቢ ደረጃ ላይ የሚገኙ አለመሆናቸውን አመልክተዋል።

4.1.2.6. የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹን የአደረጃጀት ብቃት ለመለየ ከመጽሐፉ የተገኙ ይዘቶች ትንተና፤

ይዘቶች በመምረጫ መስፈርቶች መሠረት ከተመረጡ በኋላ ተደራጅተው መቅረብ አለባቸው ። በዚህም ይዘቶች ምንም ያህል ተገቢ ቢሆኑ አደረጃጀታቸው ካላማረ የታሰበውን የባህርይ ለውጥ ሊያስገኙ እንደማይችሉ ምሁራን ያስረዳሉ (Cunningsworth 1984 Tyler 1949) ።

ለስድስተኛ ክፍል የፅህፈት ክሂል ማዳበሪያነት የቀረቡት ይዘቶች ከተከታታይነት፤ ከተለጣጣቂነትና ከውህደት መርህ አኳያ ሲታይ የሚከተለው መልክ አላቸው።

ተከታታይነትን በተመለከተ ስለ ቃላት፤ ዓረፍተነገር ፤ ስርዓተ ነጥቦች፤ ሪፖርትና ደብዳቤ አፃፃፍ በአስፈላጊ ድግግሞሽ ስለቀረቡ መስፈርቱ አለመዘንጋቱን ማየት ይቻላል። ይዘቶቹ መደጋገማቸው ብቻ ሳይሆን ለክሂሉ መዳበር የሚያበረክቱት አስተዋጽኦም ከግንዛቤ የገባ ይመስላል። ስለዚህ የተከታታይነት መስፈርት በተግባር ላይ መዋሉን ማየት ተችሏል።

በተለጣጣቂነት አኳያ ደግሞ መስፈርቱ ሙሉ በሙሉ የተጠበቀ ሆኖ አልተገኘም ምክንያቱም አንዳንድ ይዘቶች ከቀላል ወደ ከባድ ሲጓዙ አይታዩምና ነው ድርሰት ከመፃፍ በኋላ አስተዋጽኦ መንደፍ ዓረፍተነገር ከመመስረት በኋላ የእጅ ጽህፈት ማለማመድና ስፋፊ ሪፖርቶች ከመፃፍ በኋላ ስለ ሪፖርት አቀራረብ የቀረቡት ይዘቶች ይህንን የሚያረጋግጡ ናቸው።

( ለዝርዝሩ አባሪ ‘ሐ’ ይመለከቷል )

የትምህርት ይዘቶቹ የዕድገት ተከታታይነታቸውን ጠብቀው የተደራጁ ሆነው አልተገኙም ምክንያቱም ከከፍተኛ የትምህርት ክፍል ወደ ዝቅተኛው በመሄድ የተደራጁ በመሆናቸው ነው። በሌላ በኩል ከቃላት ወደ ዓረፍተነገር ከዚያም ወደ አንቀፅ መንዙ በጥቅሉ ሲታይ ከቀላል ወደ ከባድ ተደራጅቷል ማለት ያስችላል። ስርዓተ ነጥቦቹንም በተመለከተ በተናጠል ለማለማመድ የሚያስችል ሆኖ ስለተገኘ ከአጠቃላይ ወደ ተናጠል የመንዝ ባህርይን የያዘ ነው ። ስለዚህ ለክፍሉ ከቀረቡት ይዘቶች አብዛኛዎቹ በተለጣጣቂነት አኳያ የተዛቡ ሆነው ሲገኙ ጥቂት ይዘቶች በመጠኑ ተለጣጣቂነታቸው የተጠበቀ ሆነው ተገኝተዋል።

የውህደትን መርህ በተመለከተ ደግሞ ከጽህፈት ክሂል ጋር ሌሎች ክሂሎችንና የትምህርት ዘርፎችን አጣምረው ከያዙ ይዘቶች መካከል ሪፖርት ማቅረብ፣ ማስታወሻ አያያዝ፣ ሐሳብን በቃልና በጽሁፍ መግለፅ፣ ቃለመጠይቅ ማዘጋጀት ይገኙባቸዋል። አንዳንድ ይዘቶች በባህርያቸው ብዙ ዓላማዎችን ከዳር የማድረስ ብቃት አላቸው በዚህም የይዘቶቹ ጎናዊ ዝምድና አለመዘንጋቱን ለመረዳት ተችሏል።

ሰንጠረዥ 11

የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹን የአደረጃጀት ብቃት ለመለየት ለቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

ጥያቄ 4 የይዘቶቹ አደረጃጀት መስፈርቶች ምን ያህል የተጠበቁ ናቸው ብለው ያምናሉ?

| | | አማራጭ መልሶች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | | |
| | | መላሾች | | መላሾች | | መላሾች | | ድምር | |
| ተ.ቁ | የአደረጃጀት መስፈርቶች | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ተከታታይነት | 7 | 70% | 3 | 30% | - | - | 10 | 100 |
| ለ | ተለጣጣቂነት | - | - | 1 | 10% | 9 | 90% | 10 | 100 |
| ሐ | ውህደት | 5 | 50% | 5 | 50% | - | - | 10 | 100 |

ስለ ይዘቶቹ አደረጃጀት በተገኘው መረጃ መሠረት 7(70%) መላሾች ተከታታይነቱ ከፍተኛ ነው ሲሉ 3(30%) መላሾች ደግሞ መካከለኛ መሆናቸውን ገልፀዋል። ተለጣጣቂነትን በተመለከተ 1(10%) መላሾች መካከለኛ መሆኑን ሲያመለክቱ 9(90%) መላሾች ዝቅተኛ መሆኑን አመልክተዋል። በውህደት አኳያ ደግሞ 5(50%) መላሾች ከፍተኛ ነው ሲሉ 5(50%) መላሾች መካከለኛ ነው ብለዋል። በዚህም መሠረት አብዛኛዎቹ መላሾች ተከታታይነቱ ከፍተኛ መሆኑን ሲያመለክቱ ተለጣጣቂነቱ ደግሞ በዝቅተኛ ደረጃ እንደሚገኝ አመልክተዋል። ስለዚህ መረጃዎቹ በተለጣጣቂነት አኳያ ችግር እንዳለ የሚያሳዩ ሆነው ተገኝተዋል። ውህደትን በተመለከተ ግን ይህን ያህል የጎላ ችግር የሚታይበት ሆኖ አልተገኘም።

ከመጽሐፉ አዘጋጆች በተገኘው መረጃ መሠረት አንዱ የአደረጃጀት መስፈርቶቹ በሙሉ ተጠብቀዋል ሲሉ አንደኛው ግን ተከታታይነትና ውህደት በመጠኑ የተጠበቁ ሲሆኑ ተለጣጣቂነታቸው ያልተጠበቀ ይዘቶች እንዳሉባቸው አመልክተዋል።

ሰንጠረዥ 12

የጽህፈት ክፍል ይዘቶቹ የተማሪውን ደረጃ የሚመጥኑ መሆን አለመሆናቸውን ለመለየት በቀረበ ጥያቄ የተገኘ ምላሽ መግለጫ

ጥያቄ 5 የጽህፈት ክፍል ይዘቶቹ የተማሪውን ደረጃ የሚመጥኑ ይመስልዎታል?

| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥ | በመቶኛ |
| ሀ | ይመጥኑታል | 3 | 30% |
| ለ | አመጥኑትም | 7 | 70% |
| | ድምር | 10 | 100 |

ከአሥሩ መረጃ ሰጪዎች መካከል 3(30%) መላሾች ይዘቶቹ የተማሪውን ደረጃ የሚመጥኑ ናቸው ሲሉ 7(70%) መላሾች ደግሞ አይመጥኑትም ብለዋል። በአብዛኛዎቹ መላሾች መሠረትም የጽህፈት ክፍል ይዘቶቹ የተማሪውን ደረጃ የመመጠን ችግር እንደሚያሳዩ ለመረዳት ተችሏል።

ሰንጠረዥ 13.

የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ ለተማሪዎቹ ደረጃ የማይመጥኑበትን ምክንያት ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

ጥያቄ 6 በተራ ቁ. አምስት መልስዎ አይመጥኑትም ከሆነ ምክንያቱ ከተከታዩቹ የቱ ይመስልዎታል ?

| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | የተማሪዉን የቀደመ ችሎታ ስላላገናዘቡ | 5 | 71.4 |
| ለ | የተማሪዉን ፍላጎት ስላልያዙ | - | - |
| ሐ | የጽህፈትን ባህርይ በመዘንጋቱ | | |
| መ | መጠኑ ብዙ በመሆኑ | 2 | 28.6 |
| ሠ | ሌላ መልስ ካለዎት ይግለፁ | - | - |
| | ድምር | 7 | 100 |

የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ ለተማሪው ደረጃ አይመጥኑትም ካሉት ሰባት መረጃ ሰጪዎች መካከል 5(71.4%) መላሾች የተማሪውን የቀደመ ችሎታ አለማገናዘቡን በምክንያትነት ሲያቀርቡ 2(28%) መላሾች ደግሞ የጽህፈትን ባህርይ በመዘንጋቱ መሆኑን ጠቁመዋል።

በአብዛኛዎቹ መረጃ ሰጪዎች መሠረት ክሂሎች ሲመረጡ የተማሪውን ችሎታ በማገናዘብ አኳያ ችግር ያለባቸው መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

ከሁለቱ የመጽሐፍ አዘጋጆች አንዱ ይዘቶቹ በክፈል የተማሪውን ደረጃ ይመጥናሉ ሲሉ አንደው ግን አብዛኛዎቹ ይዘቶች የሚመጥኑት አለመሆናቸውን ገልፀዋል። ይህም መረጃ የተማሪውን ደረጃ የመመጠን ችግር መኖሩን የሚያሳይ ፍንጭ ሆኖ ሊታዩ ይችላል።

በመረጃው መሠረት የክፍሉ መምህራን በሙሉ በመጽሐፉ ዝግጅት አለመሳተፋቸውን ለማወቅ ተችሏል ። በዚህም የመምህራኑ በዝግጅቱ አለመካፈል ሌላው የችግሩ ምንጭ ይሆናል የሚል ግምት አሳድሯል። ይህም ወደፊት ለሚደረግ ጥናት መነሻ መሆን የሚችል ጉዳይ ነው።

የስድስተኛ ክፍል የይዘት አደረጃጀትን በተመለከተ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው አብዛኛዎቹ ይዘቶች ከዓላማ ጋር መጣጣም እንደማይታይባቸው ፤ የይዘት ምርጫ መስፈርቶቹም በተጠናከረ ሁኔታ ስራ ላይ እንዳልዋሉና በአደረጃጀትም አኳያ በተለይ የተለጣጣቂነት ችግር ጎልቶ እንደሚታይ ለመገንዘብ ተችሏል። ውህደትና ተከታታይነት ግን በመጠኑም ቢሆን ተጠብቀው ተገኝተዋል።

### 4.1.2.7. የስባተኛ ክፍል የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ዓላማን ከዳር ለማድረስ ያላቸውን ብቃት ለመለየት ከመጽሐፍ የተገኙ ይዘቶች ትንተና

ይዘቶች ዓላማን ከግብ በማድረስ ረገድ አስፈላጊ የሆኑ መለማመጃዎች መሆናቸውን በተደጋጋሚ ለመግለፅ ተሞክሯል።ዓላማ የተሳካ እንዲሆን ደግሞ ይዘቶቹ ሲመረጡ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል ብለናል። ምክንያቱም ዓላማ ለይዘት መምረጫነት የሚታይ ዋነኛ ጉዳይ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ይዘቶች ዓላማን ከዳር

በማድረስ በኩል የሚጫወቱት ሚና በቀላሉ የሚታይ መሆን እንደሌለበት መረዳት ይገባል።

የዓላማንና የይዘቶችን ስምረት በተመለከተ የሰባተኛ ክፍል የጽህፈት ክሂል ይዘቶች የሚፈለገውን ያህል ሆነው አይታዩም። ለክፍሉ ከቀረቡት ይዘቶች የሚከተሉት የአጠቃላይነት ባህርይ ያላቸው ስለሆኑ ለትንታኔ ቀርበዋል።

ቃላት ዐረፍተ ነገር መመስረት

በ ዐረፍተ ነገር ማስገት

በማጥበቅና በማላላት ዐረፍተ ነገር መመስረት

በአዳዲስ ቃላት ዐረፍተ ነገር መመስረት

ቃላትን አገናኝቶ ድርብ ከቃላትን መመስረት

ልዩ ልዩ ቃላት በ ዐረፍተ ነገር መጠቀም

አንቀፅ የተዘበራረቁ አንቀፆችን ቅደም ተከተል ማስያዝ

አንቀፆችን በትክክል ክፋፍሎ መፃፍ

አንቀፆችን ከ 5 -6 በሚደርሱ ዓ.ነገሮች ማሳጠር

የተዛቡ አንቀፆችን ማስተካከል

ዓረፍተነገር በመንስኤና በውጤት ዓ.ነ መመስረት

ዓረፍተነገር እያስፋፉ መፃፍ

ሪፖርት ሪፖርት ማቅረብ

የሪፖርት አቀራረብ ዘዴን መለማመድ

መረጃ በመሰብሰብ ሪፖርት ማቅረብ

ደብዳቤ የቤተሰብ ደብዳቤ መፃፍ

የየፉትን ደጋግሞ በማንበብ የማረም ልምድ

ጥናትና ምርምር ማድረግ

የረቂቅ ምንነትና አዘገጃጀት

ስርዓተ ነጥቦችን በትደሉበት መጠቀም

ማስታወሻ የማስቀረት ዘዴ

የእጅ ጽህፈትን ማሻሻል የእያንዳንዱን ሆሄ ቅርፅ በትክክል መፃፍ

ቃላትን በሆሄ ቅደም ተከተል ተራ ማስቀመጥ

የምንባብን ፍሬ ሐሳብ ተረድቶ መፃፍ

የሕይወት ታሪክ የራስ ሕይወት ታሪክ አፃፃፍ

ግጥም የመግጠም ልምምድ

( ለዝርዝሩ አባሪ 'ሐ' ን ይመለከቷል።)

ከእነዚህ ይዘቶች ውስጥ የአብዛኛዎቹ አቀራረብ ለሰባተኛ ክፍል ተማሪ ታስበው የተዘጋጁ አላስመሰላችውም ምክንያቱም ከተማሪው ደረጃ በታች በመሆናችው ነው።በዚህም መሠረት ስለ ቃላት ዓረፍተነገር ደብዳቤ፤ ስርዓተነጥቦች ፤ የእጅ ፅሕፈት፤የሕይወት ታሪክ የቀረቡት ይዘቶች ከተማሪው ደረጃ ዝቅ ያሉ ናችው ። ይዘቶቹ በዚህ ክፍል ደረጃ ሲቀርቡ ከፍታ ሊሰጣችው ይገባ ነበር። ተማሪው ቋንቋውን በአካባቢው ስለሚገለገልበት አውቀዋለሁ የሚል ግምት ስላለው በይዘትነት ሊቀርቡለት የሚገባችው የቋንቋው አካላት በጣም የቀለሉ ሊሆኑ አይገባችውም ተማሪው የሚያውቀውን ይዘት ያለአግባብ መደጋገሙ መሰልቸትን ስለሚያስከትል በደረጃው

የሚታሰብ ዓላማ ግቡን ሊመታ አይችልም። ከፍ ያለ ሐሳብ በጽሁፍ እንዲገልፅ ለሚጠበቅ ተማሪ የሆኔያትን ቅርፅ ለማለማመድ መሞከር ይዘትን በወቅት በማቅረብ አኳያ ችግር እንዳለ የሚያሳይ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የጥናትና ምርምር ፅሁፍ ለዚህ ክፍል ተማሪ የሚከብደው ርዕስ ሆኖ ተገኝቷል። ይህም ዓላማውን የማሳካት ብቃት ጉድለት እንዲኖረው የሚያደርግ ነው

ሰንጠረዥ 14

በክፍል ሁለት ይዘቶች የጽህፈት ክሂል ዓላማዎችን ከዳር ለማድረስ የሚያስችሉ መሆን አለመሆናቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ፤

ጥያቄ 1 የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ ዓላማን ከዳር ለማድረስ የሚያስችሉ ይመስልዎታል?

| | | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ያስችላሉ | - | - |
| ለ | በከፊል ያስችላሉ | 6 | 50% |
| ሐ | አስችሉም | 6 | 50% |
| | ድምር | 12 | 100 |

ከመረጃ ሰጪዎቹ መካከል ግማሾቹ ይዘቶቹ ዓላማን ከዳር ለማድረስ በከፊል ያስችላሉ ሲሉ ቀሪዎቹ ደግሞ አያስችሉም ብለዋል። በዚህም 6(50%) መላሾች በከፊል ያስችላሉ የሚል ምላሽ ሲሰጡ 6(50%) መላሾች ደግሞ አያስችሉም ብለዋል። በዚህም በዓላማና በይዘት መካከል ያለው መጣጣም በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

## ሰንጠረዥ 15

ይዘቶቹ ዓላማዎቹን ከዳር ለማድረስ የማያስችሉበትን ምክንያት ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

ጥያቄ 2 በተራ ቁ. አንድ መልስዎ አያስሉም የሚል ከሆነ ምክንያቱ ከተከታዩቹ ምርጫዎች የትኛው ይመስልዎታል ?

| | | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | በቁጥ | በመቶኛ |
| ሀ | አብዛኞዎቹ ይዘቶች ለክፍሉ ደረጃ የማይመጥኑ በመሆናቸው | 10 | 83.3<br>- |
| ለ | የይዘቶቹ ቅደም ተከተል የተዛባ በመሆኑ | 2 | 16.7 |
| ሐ | ሌላ መልስ ካለዎት ይግለፁ | | |
| | ድምር | 12 | 100 |

ከመረጃው ለማየት እንደተቻለው 10(83.3%) ያህሉ መላሾች ዓላማውን ከዳር ለማድረስ የማያስችሉት አብዛኞዎቹ ይዘቶች ለክፍሉ ደረጃ ባለመመጠናቸው ነው። ሲሉ 2(16.7%) ያህሉ ደግሞ ይዘቶቹ ቅደም ተከተላቸው በመዛባቱ መሆኑን ጠቁመዋል። በአብዛኞዎቹ መላሾች መሠረት ይዘቶቹን በክፍሉ ደረጃ በመመጠን ረገድ ችግር መኖሩንና ይህም በዓላማና በይዘት መካከል የመጣጣም ችግር ማስከተሉን ለመገንዘብ ተችሏል።

ከመጽሐፉ አዘጋጆች አንዱ ዓላማን ለማሳካት የማያንስ ይዘቶች መሆናቸውን ሲገልፁ አንደኛው ግን ይዘቶቹ በጣም ቀላልና ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ስለሆኑ ዓላማን ያሳካሉ ለማለት እንደማይደፍሩ ገልፀዋል። ከዚህም በመጽሐፉ ዝግጅት ወቅትም በዓላማና በይዘት ቁርኝት አኳያ ችግር መኖሩ ይታያል።

4.1.2.8 የሰባተኛ ክፍል ይዘቶች የመምረጫ መስፈርቶችን የጠበቁ መሆን አለመሆናቸው ለመለየት ከመጽሐፉ የተገኙ ይዘቶች ትንተና

ቀደም ብለን ከጠቀስናቸው የመምረጫ መስፈርቶች አኳያ ለዚህ ክፍል የቀረቡ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ሲታዩ ሁሉንም በተገቢው ደረጃ አሟልተው አልተገኙም። የይዘቶቹ ከተማሪው ደረጃ በታች መሆን መስፈርቶቹን በተገቢው መንገድ ስራ ላይ የማዋል ችግር መኖሩን የሚጠቁም ሆኖ ተገኝቷል። ተማሪው ሊሞክራቸው የማይችላቸው ይዘቶችም ይህንኑ ያመለክታሉ።

የይዘት መምረጫ መስፈርቶች እርስ በርሳቸው የተደጋገፉ በመሆናቸው አንደኛው በአንደኛው ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል። ምክንያቱም ለአንድ ክፍል ደረጃ ተገቢ ያልሆነ ይዘት አስፈላጊ ፣ አስደሳች ለመማር አመቺነት ያለው ሊሆን አይችልምና ነው። ከሁሉም በላይ ግን የይዘቶች ተተግባሪ መሆን ሊታሰብበት የሚገባ ነጥብ ነው። በዚህም መሠረት ይዘቶቹን በተማሪው ደረጃ በመምረጥ ረገድ የጎላ ችግር እንዳለ ማስተዋል ተችሏል።

(ዝርዝሩን ከአባሪ 'ሐ'ን ይመለከቷል)

ስንጠረዥ 16

የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ የመምረጫ መስፈርቶችን የጠበቁ መሆን አለመሆናቸውን ለመለየት ለመምህራኑ ለቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

ጥያቄ 3 የይዘቶቹ አደረጃጀት መስፈርቶች ምን ያህል የተጠበቁ ናቸው ብለው ያምናሉ ?( 3 ከፍተኛ 2 መካከለኛ 1 ዝቅተኛ )

| | | አማራጭ መልሶች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | | |
| | | መልሶች | | መልሶች | | መልሶች | | ድምር | |
| ተ.ቁ | የይዘት መምረጫ መስፈርቶች | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ተገቢነት | - | - | 2 | 16.7 | 10 | 83.3 | 12 | 100 |
| ለ | አስፈላጊነት | - | - | 3 | 25 | 9 | 75 | 12 | 100 |
| ሐ | ዘላሐእት | - | - | 3 | 25 | 9 | 75 | 12 | 100 |
| መ | አስደሳችነት | - | - | 1 | 8.3 | 11 | 91.7 | 12 | 100 |
| ሠ | ለመማር ያላቸው አመቺነት | - | - | - | - | 12 | 100 | 12 | 100 |
| ረ | ሌላ ካለ ይገለፅ | - | - | - | - | - | - | - | - |

ከመረጃ ሰጪዎች በተገኘው ምላሽ መሠረት በአብዛኛዎቹ መላሾች ሁሉም መስፈርቶች በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ለመገንዘብ ተችሏል። በዚህም መሠረት 9(75%) መላሾች የይዘቶቹን አስፈላጊነትና ዘላቂነት በዝቅተኛ ደረጃ እንደሚገኙ ሲያመለክቱ 10(93.3%) መላሾች ደግሞ ተገቢነታቸው ዝቅተኛ መሆኑን አሳይተዋል 11(91.7%) መላሾች የአስደሳችነታቸውን ዝቅተኛነት ሲያመለክቱ 12(100) መላሾች

ደግሞ ለመማር ያላቸው አመቺነት ዝቅተኛ መሆኑን ጠቁመዋል  በዚህም መረጃ መሠረት ይዘቶቹን በመምረጥ ረገድ ችግር መኖሩን ለመገንዘብ ይቻላል።

የመጽሐፉ አዘጋጆች ሁለቱም በይዘት መምረጫ መስፈርቶች መመረጣቸውን የሚጠራጠሩ መሆናቸውን ገልፀዋል። ከገለፃቸውም መርሐ ትምህርቱን ብቻ መሠረት በማድረግ በይሁን ይሁን ማዘጋጀታቸውን ለመረዳት ተችሏል።  ስለዚህ የይዘት መምረጫ መስፈርቶቹን ጠቀሜታ በማስተዋል ረገድ ጉድለት መኖሩን ለመረዳት ተችሏል።

4.1.2.9 የጽህፈት ክሂል ይዘቶችን የአደረጃጀት ብቃት ለመለየት ከመጽሐፉ የተገኙ ይዘቶች ትንተና

አንድን ዓላማ ከግብ ያደርሳሉ ተብለው የሚታሰቡ ይዘቶች በወጉ ተደራጅተው ካልቀረቡ በተማሪው የትምህርት አቀባበል ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ እንደሚችሉ ቀደም ባለው ምዕራፍ ለመግለፅ ተሟክሯል። ስለዚህ የተመረጡት ይዘቶች በተማሪው ደረጃ ተመጥነው ከቀላል ወደ ከባድ በመሄድ መደራጀት ይገባቸዋል። ለዚህም የይዘት አደረጃጀት መስፈርቶችን መሠረት ያደርጋሉ።

የሰባተኛ ክፍል የጽህፈት ክሂል አደረጃጀት ከተከታታይነት መስፈርት አኳያ ሲታይ በአስፈላጊ ድግግሞሽ የቀረቡ በርካታ ይዘቶችን ያካተተ ሆኖ ተገኝቷል። ስለ ቃላት ፣ ዓረፍተነገር፣ ሪፖርት አንቀፅ ፣ ስርዓተ ነጥብ ፣ የእጅ ፅህፈትና ግጥም በተለያዩ ጊዜያት ተማሪው እየደጋገመ እንዲያያቸው ተደርጓል።  በዚህ በኩል መስፈርቱ የተጠበቀ ቢሆንም የተደጋገሙት ይዘቶች በርግጥ ለተማሪው ደረጃ ይመጥናሉን? የሚለው ጥያቄ የመስፈርቱን አተገባበር ችግር የሚያሳይ ነው።

ተለጣጣቂነትን በተመለከተ ይዘቶቹ እርስ በርሳቸው ተደጋግፈው ሲሄዱ አይስተዋልም። አንቀፅ ፣ ሪፖርት ፣ ጥናትና ምርምር፣ ማስታወሻ ግጥም እንዲፅፉ

የሚያለማምዱት ይዘቶች መካከል የሆኄያትን ቅርፅ ስለማስለየት የሚያወሳ ገብቶ ይታያል። በዚህም አደረጃጀቱ የተዛባ መሆኑን ማየት ይቻላል። ይህም ተማሪውን በራሱ መተማመን እንዳይኖረው ሊያደርገው ይችላል። በተጨማሪም ሪፖርት እንዲያቀርብ የሚያደርገው ይዘት ቀድሞሲገኝ ስለሪፖርት አቀራረብ ዘዴ የሚያሳየው ይዘት ግን በኋላ ሆኖ ታይቷል። ሪፖርት ለመፃፍ ዘዴውን ቀድሞ ማወቁ የሚገባ ነበር። በዚህም ይዘቶቹን አንዱን ላንዱ መሠረት አድርጎ በማደራጀቱ አንፃር ችግር እንዳለ ለመረዳት ይቻላል።

ውህደትን በተመለከተ ደግሞ ሌሎች ክሂሎችንና የትምህርት ዘርፎችን ከጽህፈት ጋር አጣምረው የያዙ ይዘቶች እንዳሉባቸው ለማወቅ ተችሏል። ሪፖርት ማቅረብ፤ መረጃ መሰብሰብ፤ የፃፉትን ደጋግሞ በማንበብ የማረም ልምድ፤ ጥናትና ምርምር ማድረግ ማስታወሻ የማስቀረት ዘዴና የምንባብን ፍሬሐሳብ ተረድቶ መፃፍ የሚሉት ይዘቶች በባህርያቸው የተለያዩ ክሂሎችን ሊያለማምዱና ከተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ጋር ሊጣመሩ የሚችሉ ሆነው ተኝተዋል። በውህደት ረገድ መስፈርቱ በስራ ላይ ውሏል ለማለት ይቻላል። ስለዚህ በይዘቶች ጎናዊ ዝምድና በኩል የጎላ ችግር አይታይም

## ሰንጠረዥ 17

የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹን የአደረጃጀት ብቃት ለመለየት ለቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

ጥያቄ 4 የይዘቶቹ አደረጃጀት መስፈርቶች ምን ያህል የተጠበቁ ናቸው ብለው ያምናሉ?

| ተ.ቁ | የአደረጃጀት መስፈርቶች | አማራጭ መልሾች | | | | | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | | |
| | | መላሾች | | መላሾች | | መላሾች | | | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ተከታታይነት | - | - | 10 | 83.3 | 2 | 16.7 | 12 | 100 |
| ለ | ተለጣጣቂነት | - | - | 1 | 8.3 | 11 | 91.7 | 12 | 100 |
| ሐ | ውህደት | - | - | 10 | 83.3 | .2 | 16.7 | 12 | 100 |

ተከታታይነትን በተመለከተ 10(83.3%) መላሾች መካከለኛ ደረጃ ላይ መገኘቱን ሲያመለክቱ 2(16.7%) መላሾች ደግሞ ዝቅተኛ ነው ብለዋል። በተለጣጣቂነትም አኳያ 1(8.3%) መላሾች መካከለኛ መሆኑን ሲያመለክቱ 11(91.7%) መላሾች ዝቅተኛ እንደሆነ ጠቁመዋል። 10(83.3%) መላሾች ውህደቱ መካከለኛ ነው ሲሉ 2(16.7%) ያህሉ ደግሞ ዝቅተኛ መሆኑን ገልፀዋል። በመረጃውም መሠረት አብዛኛዎቹ መላሾች ተከታታይነትና ውህደት በመካከለኛ ደረጃ ይገኛል ሲሉ ተለጣጣቂነትን ደግሞ በዝቅተኛ ደረጃ እንደሚገኝ አሳይተዋል። ስለዚህ በተለጣጣቂነት አኳያ የአደረጃጀት ችግር መኖሩን የሚጠቁም መረጃ ሆኖ ተገኝቷል።

አንዳንድ መምህራን በሰጡት ተጨማሪ አስተያየትም የዚህ ክፍል ይዘት ከክፍሉ ደረጃ በታች መሆኑን ጠቁመዋል። አንድ መረጃ ሰጪም አደረጃጀቱ ለአሠራር አመቺ ባለመሆኑ የየራሳቸውን ቅደም ተከተል የሚያወጡ መምህራን መኖራቸውን ጠቁመው ይህ ደግሞ ወጥ አሠራርን ለመከተል እንደማያመች አውስተዋል።

ከመጽሐፉ አዘጋጆች አንዱ ተለጣጣቂነት ላይ ችግር እንዳለ የታወቀው ከዝግጅቱ በኋላ መሆኑን ጠቅሰዋል። በዚህም መሠረት የመስፈርቱን ጠቀሜታ ተረድቶ በስራ ላይ የማዋል ችግር እንዳለ መረዳት ተችሏል። አንደኛው መረጃ ሰጪ ደግሞ ተለጣጣቂነቱ ያልተጠበቀ አደረጃጀት መሆኑን ገልፀዋል። ሁለቱም መላሾች ግን በተከታታይነትና በውህደት አኳያ ችግር አለመኖሩን ገልፀዋል።

ሰንጠረዥ 18

ይዘቶቹ የተማሪውን ደረጃ የሚመጥኑ መሆን አለመሆናቸውን ለመለየት ለቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

ጥያቄ 5 የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ የተማሪውን ደረጃ የሚመጥኑ ይመስልዎታል ?

| | | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | በቁጥ | በመቶኛ |
| ሀ | ይመጥኑታል | 2 | 16.7 |
| ለ | አይመጥኑትም | 10 | 83.3 |
| | ድምር | 12 | 100 |

በተገኘው መረጃ መሠረት 2(16.7%) መላሾች ይዘቶቹ የተማሪውን ደረጃ ይመጥናሉ ሲሉ 10(83.3%) መላሾች ደግሞ አይመጥኑም ብለዋል። በአብዛኛዎቹ መረጃ ሰጪዎች መሠረት ይዘቶቹ በተማሪው ደረጃ መመጠናቸው የሚያጠያይቅ ሆኖ ይታያል።

## ሰንጠረዥ 19

የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ ለተማሪዎቹ ደረጃ የማይመጥኑበትን ምክንያት ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

በተራ ቁ. አምስት መልስዎ አይመጥኑትም ከሆነ ምክንያቱ ከተከታዮቹ የቱ ይመስልዎታል ?

| | | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | በቁጥ | በመቶኛ |
| ሀ | የተማሪውን የቀደመ ችሎታ ስላላገናዘቡ | 9 | 90% |
| ለ | የተማሪውን ፍላጎት ስላልያዙ | - | - |
| ሐ | የጽህፈት ባህርይ በመዘንጋቱ | 1 | 10% |
| መ | መጠኑ ስለበዛ | - | - |
| ሠ | ሌላ መልስ ካለዎት ይግለፁ | - | - |
| | ድምር | 10 | 100 |

አይመጥኑትም ካሉት አስር መላሾች መካከል 9(90%) ያህሉ የተማሪውን የቀደመ ችሎታ ያላገናዘቡ ይዘቶች በመሆናቸው መሆኑን ሲገልፁ 1(10%) መላሾች ደግሞ የጽህፈት ባህርይ በመዘንጋቱ መሆኑን በምክንያትነት አቅርበዋል። በአብዛኞዎቹ ተጠያቂዎች መረጃነት መሠረት የተማሪውን የቀደመ ችሎታ በማጥናት በኩል ችግር እንዳለ ለመገንዘብ ተችሏል።

ከመጽሐፉ አዘጋጆች አንዱ ይዘቶቹ ተማሪውን ደረጃ በመጠኑ ይመጥናሉ ሲሉ አንደኛው ግን ከደረጃው በታች የሆኑ ይዘቶች ስለሚበዛባቸው ይመጥናሉ ለማለት እንደሚቸገሩ ገልፀዋል። አክለውም በተማሪው አኳያ በቂ ጥናት አለመደረጉን አመልክተዋል። ከሁለቱም መረጃ ሰጪዎች ምላሽ የተማሪዎቹን ደረጃ የማይመጥኑ ይዘቶች በብዛት መኖራቸውን ለማየት ይቻላል።

የሰባተኛ ክፍልን የጽህፈት ክሂል አደረጃጀት በተመለከተ በተሰበሰቡት መረጃዎች አማካይነት ለመገንዘብ እንደተቻለው ይዘቶቹ በአብዛኛው ከተማሪው ደረጃ በታች በመሆናቸው የይዘት ምርጫ መስፈርቶቹን በመጠበቅ ረገድ ችግር መኖሩን ያሳያሉ። በተጨማሪም የይዘት አደረጃጀት መስፈርቶቹን በተመለከተም ውህደትና ተከታታይነት በመጠኑ ተጠብቀው ሲታዩ በተለጣጣቂነት አኳያ ግን የጎላ ችግር እንዳለ መረጃዎቹ የሚጠቁሙ ሆነው ተገኝተዋል። እንዲሁም የመምህራኑ በመጽሐፉ ዝግጅት አለመሳተፍም ሊላው የችግሩ ምንጭ ይሆናል የሚል ግምት አሳድሯል።

4.1.2.10 የስምንተኛ ክፍል የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ዓላማን ከዳር ለማድረስ ያላቸውን ብቃት ለመለየት ከመጽሐፉ የተገኙ ይዘቶች መረጃዎች ትንተና

ቀደም ባሉት የጽሁፉ ንዑስ ክፍሎች ለማመልከት እንደተሞከረው ዓላማ ግቡን እንዲመታ ከተፈለገ የሚመረጡት ይዘቶች በተማሪው ደረጃ ተመጥነው ተተግባሪ መሆን መቻል አለባቸው። የትምህርት ዓላማዎችና ይዘቶች ስነልቡናዊና ተጠየቃዊ በሆነ መልክ መቅረብ እንዳለባቸው ይገልፃሉ። (Taba 1962 Tyler 1949) በዚህም መሠረት ይዘቶች ዓላማን እንዲያሳኩ ሊጓዙባቸው የሚያስችሉ ሆነው መቅረብ አለባቸው። ለምሳሌ፤ የጽህፈትን ክሂል ግብ ለማድረስ ተማሪውን በደረጃው ጽህፈት የሚያለማምዱት መሆን አለባቸው። ምክንያቱም ተማሪው በተግባር ሊያውላቸው የማይችላቸው ይዘቶች ከዓላማ ጋር የሚስምሩ አይሆኑምና ነው።

ለስምንተኛ ክፍል የቀረቡትን የጽህፈት ክሂል ይዘቶች በማጤን ከዓላማ ጋር ስላላቸው መጣጣም ቀጥለን ለማየት እንሞክር።

ቃላት - ዐረፍተ ነገር መስራት

የአንድ ቃል የተለያየ ትርጉም በዐረፍተ ነገር ማስገባት

ዐረፍተ ነገር - አስተካክሉ መፃፍ

ምስረታ

የተነጣጠሉ ሐሳቦችን በማገናኘት ዐረፍተ ነገር መመስረት

እየጠበቁና እየላሉ ሊነበቡ የሚችሉ ቃላት የያዙ ዐረፍተ ነገሮችን መመስረት

ማስተካከል

በመንስኤና በውጤት መከፋፈልና መፃፍ

ድርሰቶችን መፃፍ የድርሰቶችን ጭብጥ መግለፅ

የፈጠራ ጽሁፍ መፃፍ

የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ የግለሰብ ሕይወት ታሪክ መፃፍ

የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን መተንተን

ያዩትንና የሰሙትን የሊብነት ተግባር በጽሁፍ ማቅረብ

የሰዎችን ሃሳብ ጠይቆ በጽሁፍ ማቅረብ

አጭር ግጥም መፃፍ

አንቀፅ - አንቀፅን በ30 መስመር ማስፋፋት

- የአንቀፁን ዋና ሐሳብ በራስ አማርኛ በጽሁፍ ማቅረብ

- ዝርዝር ሐሳቦችን በአንድ ዋና ዐረፍተ ነገር ማጠቃለል

ስርዓተ ነጥቦችን ማስቀመጥ

( ለዝርዝሩ አባሪ 'ሐ' ይመለከቷል )

ከነዚህ ይዘቶች መካከል ዓላማን ሊያሳኩ የሚችሉና የማይችሉ እንደሚገኙባቸው ለማየት ተችሏል። በዚህም መሠረት ስለ ቃላት ፤ ዓረፍተነገር ፤ የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ ፤ ያዩትንና የሰሙትን የሌብነት ተግባር በጽሁፍ መግለፅ ፤ የሰዎችን ሐሳብ ጠይቆ በጽሁፍ ማቅረብ ፤ አንቀፅና ስርዓተ ነጥቦች የቀረቡት ይዘቶች በዚህ ክፍል ደረጃ ሊተገበሩ የሚችሉ በመሆናቸው ዓላማን ከዳር ሊያደርሱ የሚችሉ ናቸው። ምክንያቱም በሶስቱ ክፍሎች ያዳበረው ዕውቀት እነዚን ይዘቶች ለመተግበር አያንስም ነው።

የድርሰቶችን ጭብጥ መግለፅ፤ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን መተንተንና የፈጠራ ጽሁፍ መፃፍን የሚያመለክቱት ይዘቶች በትችት የትምህርት ክፍል የሚመደቡ ናቸው። ስለሆነም መፍረድን፤ አስተያየት መስጠትንና መተንተንን ይጠይቃሉ። የዚህ ዓይነት የትምህርት ይዘቶች ደግሞ መቅረብ ያለባቸው ለከፍተኛ ደረጃ ተማሪዎች ነው። (Bloom1956) ስለዚህ እነዚህ ይዘቶች ለክፍሉ ተማሪ የማይመጥኑ ናቸው የሚል ግምት አሳድሩዋል። ስለሆነም ከይዘቶቹ መካከል ከተማሪው ደረጃ በላይ የሆኑ ይዘቶች በመኖራቸው ዓላማን የማሳካት ብቃታቸው ችግር እንደሚኖረው ለመገንዘብ ያስችላል።

ሰንጠረዥ 20

በክፍል ሁለት ይዘቶቹ ዓላማዎችን ከዳር ለማድረስ የሚያስችሉ መሆን አለመሆናችውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

ጥያቄ 1 የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ ዓላማን ከዳር ለማድረስ የሚያስችሉ ይመስልዎታል ?

| | | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | በቁጥ | በመቶኛ |
| ሀ | ያስችላሉ | - | - |
| ለ | በከፊል ያስችላሉ | 8 | 66.6 |
| ሐ | አያስችሉም | 4 | 34.4 |
| | ድምር | 12 | 100 |

መጠይቁን ከሞሉት አሥራሁለት መምህራን 8(66.6%) መላሾች ይዘቶቹ ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉት በከፊል እንደሆነ ሲገልፁ 4(33.4%) መላሾች ደግሞ ዓላማን ከግብ ሊያደርሱ እንደማያስችሉ አመልክተዋል። ከመረጃው ለመገንዘብ እንደተቻለው በይዘቶቹና በዓላማዎቹ መካከል አልፎ አልፎ ያለመጣጣም ችግር እንዳለ ነው።

## ሰንጠረዥ 21

ይዘቶቹ ዓላማዎቹን ከዳር ለማድረስ የማያስችሉበትን ምክንያት ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ፤

ጥያቄ 2 በተራ ቁ. አንድ መልስዎ አያስችሉም የሚል ከሆነ ምክንያቱ ከተከታዮቹ ምርጫዎች የትኛው ይመስልዎታል ?

| | | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | በቁጥ | በመቶኛ |
| ሀ | አብዛኛዎቹ ይዘቶች ለክፍሉ ደረጃ የማይመጥኑ በመሆናቸው | 9 | 75 |
| ለ | የይዘቶቹቅደም ተከተል የተዛባ በመሆኑ | 3 | 25 |
| ሐ | ሌላ መልስ ካለዎት ይግለፁ | - | - |
| | ድምር | 12 | 100 |

ይዘቶቹ ዓላማውን ዳር ለማድረስ የማይችሉበትን ምክንያት 9(75%) ያህሉ ተጠያቂዎች አብዛኛዎቹ ይዘቶች ለክፍሉ ደረጃ የማይመጥኑ በመሆናቸው እንደሆነ ሲገልፁ 3(25%) ያህሉ ደግሞ የይዘቶቹ ቅደም ተከተል የተዛባ መሆኑን አመልክተዋል። ከአብዛኛዎቹ መላሾች ለመረዳት እንደተቻለው ለክፍሉ ደረጃ የማይመጥኑ ይዘቶች በዓላማና በይዘት መካከል የአለመጣጣም ችግር ማስከተላቸውን ነው።

ከመጽሐፉ አዘጋጆች አንዱ የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ በሙሉ ዓላማውን የሚያሳኩ ናቸው ሲሉ አንደኛው መላሽ ደግሞ አንዳንድ የተማሪውን ችሎታ ያላገናዘቡ ይዘቶች በመኖራቸው ሁሉም ዓላማውን ያሳካሉ የሚል እምነት እንደሌላቸው ገልፀዋል።

4.1.2.11 የስምንተኛ ክፍል ይዘቶች የመምረጫ መስፈርቶችን የጠበቁ መሆን አለመሆናቸውን ለመለየት ከመጽሐፉ  የተገኙ ይዘቶች  ትንተና

የዚህ ክፍል የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ከመምረጫ መስፈርቶች አኳያ ሲታዩ አንዳንድ ችግሮች ተስተውለውባቸዋል።

ቀደም ተብሎ በተጠቆመው መሠረት የይዘት መምረጫ መስፈርቶቹ ተያያዥነት እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል። በክፍሉ ተማሪ ሊሞክሩ የሚችሉ ይዘቶች በመጠኑም ቢሆን ተገቢ አስፈላጊና ለመማር አመቺነት ያላቸው ሊባሉ ይችላሉ። አስደሳችነታቸውም ይዘቶቹ ለተማሪው ካላቸው ጠቀሜታ አኳያ የሚታይ ነው። በዚህም መሠረት ከስምንተኛ ክፍል የጽህፈት ክሂል ይዘቶች መካከል ስለቃላት ፤ ዓ.ነገሮች ፤ የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ ፤ያዩትንና የሰሙትን የሌብነት ተግባር በጽሁፍ መግለፅ. የሰዎችን ሐሳብ ጠይቆ በጽሁፍ ማቅረብና ስርዓተ ነጥቦች የሚያውሱት ይዘቶች ተገቢነት፤ ዘላቂነት፤ አስፈላጊነት፤ አስደሳችነትና ለመማር አመቺ የመሆንን መስፈርት በመጠቀም የተመረጡ ናቸው ሊባሉ ይችላሉ። የቀሩት ይዘቶች ግን ከተማሪው ደረጃ እልፍ ያሉ በመሆናቸው በይዘት መምረጫ መስፈርቶች ተመርጠዋል ለማለት የሚያስደፍሩ ሆነው አልታዩም።

( ለዝርዝሩ አባሪ ‘ሐ’ ይመለከቷል )

ሰንጠረ ዥ22

የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ የመምረጫ መስፈርቶችን የጠበቁ መሆን አለመሆናቸውን ለመለየት ለመምህራኑ ለቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

ጥያቄ 3 የይዘቶ ቹ አደረጃጀት መስፈርቶቹ ምን ያህል የተጠበቁ ናቸው ብለው ያምናሉ ? (3 ከፍተኛ 2 መካከለኛ 1 ዝቅተኛ)

| | | አማራጭ መልሾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | | |
| | | መላሾች | | መላሾች | | መላሾች | | ድምር | |
| ተ.ቁ | የይዘት መምረጫ መስፈርቶች | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ተገቢነት | - | - | 7 | 58.4 | 5 | 41.6 | 12 | 100 |
| ለ | አስፈላጊነት | - | - | 5 | 41.6 | 7 | 58.4 | 12 | 100 |
| ሐ | ዘላቂነት | - | - | 4 | 33.4 | 8 | 66.6 | 12 | 100 |
| መ | አስደሳችነት | - | - | 3 | 25 | 9 | 75 | 12 | 100 |
| ሠ | ለመማር ያላቸው አመቺነት | - | - | 2 | 16.8 | 10 | 83.4 | 12 | 100 |
| ረ | ሌላ ካለ ይገለፅ | - | - | - | | - | - | - | - |

ለመጠይቁ ምላሽ ከሰጡት አስራሁለት መምህራን መካከል አብዛኛዎቹ መላሾች አስፈላጊነት፤ ዘላቂነት፤ አስደሳችነትና ለመማር ያላቸው አመቺነት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዳለ ሲያመለክቱ ተገቢነት ደግሞ በመካከለኛ ደረጃ ላይ መሆኑን አሳይተዋል። በመረጃዎቹ መሠረት የይዘት መምረጫ መስፈርቶቹን በአግባቡ ስራ ላይ በማዋል ረገድ ችግር እንዳለባቸው ለመረዳት ይቻላል።

የመጽሐፉ አዘጋጆች ሁለቱም የይዘት መምረጫ መስፈርቶች አለመፐበቃቸውን ገልፀዋል። አንዱ በሰጡት ተጨማሪ አስተያየትም ለዚህ ችግር መፈጠር ዋነኛው ምክንያት በመርሐ ትምህርት አዘጋጆችና በመጽሐፍ አዘጋጆች መካከል የተቀናጀ

አሠራር አለመኖሩ መሆኑን ገልፀዋል። ከዚህም ለመረዳት የሚቻለው በቅንጅት ለመስራት አለመሞከሩ ተጨማሪ ችግር እንደፈጠረ ነው።

4.1.2.12 የጽህፈት ክሂል ይዘቶችን የአደረጃጀት ብቃት ለመለየት ከመጽሐፉ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ይዘቶች ተደራጅተው የመቅረባቸውን ጠቀሜታ በተለያዩ የጽሁፉ ክፍሎች ለማውሳት ተሞክሯል። የይዘቶች አደረጃጀት በመማር ማስተማር ብቃት እንዲሁም በተማሪው የትምህርት አቀባበል ላይ አወንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል (Tyler 1949)

በዚህም መሠረት የስምንተኛ ክፍል ይዘቶችን አደረጃጀት ለመቃኘት ስንሞክር ተከታታይነትን በተመለከተ ስለቃላት ፤ ዓረፍተነገር ፤ አንቀፅና ስርዓተነጥቦች የቀረቡት ይዘቶች እየተደጋገሙ ቀርበው ይታያሉ

(ለዝርዝሩ አባሪ ‘ሐ’ ይመለከቷል )

ስለዚህ መስፈርቱ ያልተዘነጋ ሆኖ ተገኝቷል። እነዚህ ይዘቶችም ለጽህፈት ክሂል አስፈላጊ በመሆናቸው በተከታታይነት መቅረባቸው የመስፈርቱን ተግባር ላይ መዋል የሚያመለክት ነው።

በተለጣጣቂነት አኳያም አንዳንድ ይዘቶች መስፈርቱን ጠብቀው በመገኘት በኩል ችግር እንዳለባቸው ለመረዳት ተችሏል። ከዓረፍተነገር ምስረታ ወደ ድርሰት ተሸጋግሮ ይታያል። አንቀፅ የሚመጣው በስተመጨሻ ነው። ከዓረፍተነገር ቀጥሎ አንቀፅ አለመቅረቡ ከቀላል ወደ ከባድ በመሄድ ረገድ ችግር እንዳለ ያመለክታል። የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን መተንተን የሚለው ርዕስ ደግሞ ከሚታወቅ ወደ

ማይታወቅ የሚያስኬድ ሆኖ አልተገኘም። ስለዚህ ተለጣጣቂነት በጥያቄ ውስጥ የሚወድቅ ይሆናል።

የውህደትን መርህ አስመልክቶ ከጽህፈት ክሂል ጋር ሌሎች ክሂሎችንና የትምህርት ዘርፎችን ሊያለማምዱ የሚችሉ ይዘቶች እንደሚገኙባቸው ለማጤን ተችሏል። በዚህም መሠረት የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ ያዩትንና የሰሙትን የሌብነት ተግባር በጽሁፍ ማቅረብ፤ የሰዎችን ሃሳብ ጠይቆ በጽሁፍ ማቅረብ፤ እየጠበቁና እየሳሉ ሊነበቡ በሚችሉ ቃላት ዐረፍተነገር መመስረት የጽሁፍ መግለጫዎችን ወደ መረጃ ሰንጠረዥ መለወጥ የተባሉት ይዘቶች በባህሪያቸው ውህደትን የተከተሉ ናቸው። ምክንያቱም ከጽህፈት ክሂል ባሻገር ከሌሎች ክሂሎችና ማህበራዊ ጉዳዮች ጋር የተጣመሩ በመሆናቸው ነው። የክሂሎች ጥምረትና ከሌሎች የትምህርት ዘርፎች ጋር የሚደረገው ተዋህዶ ከጎናዊ አደረጃጀት የሚገኝ ስነትምህርታዊ ፋይዳ ነው (Taba 1962) ።

## ሰንጠረዥ 23

የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹን የአደረጃጀት ብቃት ለመለየት ለመምህራኑ በቀረበ ጥያቄ የተገኘ ምላሽ መግለጫ

ጥያቄ 4 የይዘቶቹ አደረጃጀት መስፈርቶች ምን ያህል የተጠበቁ ናቸው በለው ያምጡ?

| ተ.ቁ | የአደረጃጀት መስፈርቶች | አማራጭ መልሾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | ድምር | |
| | | መላሾች | | መላሾች | | መላሾች | | | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ተከታታይነት | - | - | 8 | 66.6 | 4 | 33.4 | 12 | 100 |
| ለ | ተለጣጣቂነት | - | - | 2 | 16.8 | 7 | 10 | 12 | 100 |
| ሐ | ውህደት | 4 | 33.4 | 8 | 66.6 | - | - | 12 | 100 |

ከላይ በሚታየው መረጃ መሠረት 8 (66.6%) መላሾች ውህደትና ተከታታይነት በመካከለኛ ደረጃ እንደሚገኙ ሲያመለክቱ 4 (33.4% ) መላሾች ተከታታይነት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዳለ አሳይተዋል። 10(83.4%) መላሾች ተለጣጣቂነት ዝቅተኛ ነው። ሲሉ 2(16. 8% ) መላሾች ደግሞ መካከለኛ እንደሆነ አሳይተዋል። 4 ( 33.4%) መላሾች የውህደትን በከፍተኛ ደረጃ ላይ መገኘት ጠቁመዋል።

በአብዛኞቹ መላሾች መሠረት የተለጣጣቂነት አደረጃጀት ላይ ችግር መኖሩን መገንዘብ ተችሏል ውህደትና ተከታታይነትን በተመለከተ ግን መስፈርቶቹ በመጠኑም ቢሆን ሥራ ላይ እንደዋሉ የሚያመለክት መረጃ ሆኖ ተገኝቷል።

ከመጽሐፉ አዘጋጆች አንዱ የይዘቶቹ አደረጃጀት በተቻለ መጠን ተጠብቆ የቀረበ መሆኑን በደፈናው ሲገልፁ አንደኛው መላሽ ግን ውህደትንና ተከታታይነት በመጠኑ ቢጠበቁም በተለጣጣቂነት አኳያ ግን መዛባት ስለሚታይ ከሁሉም የባሰ ችግር መኖሩን ገልፀዋል። በተጨማሪም የይዘቶቹ መጠን በርካታ በመሆኑ መምህራን የቱን ይዘው የቱን እንደሚለቁ ግራ የሚያጋባ መሆኑን አብራርተዋል።

ሰንጠረዥ 24

ይዘቶቹ የተማሪውን ደረጃ የሚመጥኑ መሆን አለመሆናቸውን ለመለየት ለቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

ጥያቄ 5 የጽሕፈት ክሂል ይዘቶቹ የተማሪውን ደረጃ የሚመጥኑ ይመስልዎታል ?

| 5 | | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | በቁጥ | በመቶኛ |
| ሀ | ይመጥኑታል | 3 | 25.0 |
| ለ | አይመጥኑትም | 9 | 75.0 |
| | ድምር | 12 | 100 |

ከአሥራ ሁለቱ ተጠያቂዎች መካከል 3(25%) መላሾች ይዘቶቹ የተማሪውን ደረጃ ይመጥናሉ ሲሉ 9(75%) መላሾች ደግሞ እንደማይመጥኑ ገልፀዋል። በአብዛኛዎቹ መላሾች መሠረት የትምህርት ይዘቶቹ ተማሪውን በመመጠን ረገድ ችግር እንዳለባቸው የሚጠቁሙ መረጃዎች ሆነው ተገኝተዋል።

ሰንጠረዥ 25

የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ ለተማሪዎቹ ደረጃ የማይመጥኑበትን ምክንያት ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

ጥያቄ 5 በተራ ቁ. አምስት መልስዎ አይመጥኑትም ከሆነ ምክንያቱ ከተከታዮቹ የቱ ይመስልዎታል?

| | | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | የተማሪውን የቀደመ ችሎታ ስላላገናዘቡ | 6 | 66.7 |
| ለ | የተማሪውን ፍላጎት ስላልያዙ | 2 | 22.3 |
| ሐ | የጽህፈት ባህርይ በመዘንጋቱ | 1 | 11.0 |
| መ | መጠኑ ስለበዛ | - | - |
| ሠ | ሌላ መልስ ካለዎት ይግለፁ | - | - |
| | ድምር | 9 | 100 |

ይዘቶቹ አይመጥኑትም ካሉት ዘጠኝ መረጃ ሰጪዎች መካከል አብዛኛውን ቁጥር የያዙት የተማሪውን የቀደመ ችሎታ ያላገናዘቡ በመሆናቸው መሆኑን በምክንያትነት አቅርበዋል። በዚህም መረጃ መሠረት የተማሪውን ችሎታና ደረጃ አጥንቶ ይዘቶቹን በመመጠን ረገድ ችግር እንዳለበት መረዳት ተችሏል።

የመጽሐፉ አዘጋጆችም አንደኛው ይመጥኑታል የሚል ምላሽ ሲሰጡ አንደኛው ግን በዝግጅቱ ወቅት በእርከኑ ውስጥ መነሳት አለባቸው በተባሉ ይዘቶች ላይ እንጂ ተማሪውን በሚመጥኑት ላይ አለመተኮሩን ገልፀው ስለተማሪው በቂ ጥናት አለመደረጉንም አመልክተዋል። በተጨማሪም ዝግጅቱ የአራተኛና የስምንተኛ ክፍል

በመሆኑ የተማረውን ዳራዊ እውቀት የሚያሳያችው ሁኔታ አለመኖሩን በመጠቆም ይህም ለችግሩ መፈጠር ያለውን አስተዋጽዖ አመልክተዋል።

ሰንጠረዥ 26

መምህራኑ በመጽሐፉ አዘጋጅነት መሳተፍ አለመሳተፋቸውን ለማወቅ ለቀረበ ጥያቄ የተሰጡ ምላሽ መግለጫ፤

ጥያቄ 7 የመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅተው ያውቃሉ ?

| | ኜ | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | በቁጥ | በመቶኛ |
| ሀ | አዘጋጅቻለሁ | - | - |
| ለ | አላዘጋጀሁም | 46 | 100 |
| | ድምር | 46 | 100 |

በተገኘው መረጃ መሠረት ከመምህራኑ መካከል አንድም በዝግጅቱ የተሳተፉ አለመኖሩ ሊታወቅ ችሏል። ይህም በመጽሐፉ ውስጥ ሲያዩ የይዘት አደረጃጀት ችግሮች አስተዋጽኦ ይኖረዋል የሚል ግምት አሳድሯል።

ሰንጠረዥ 27

መምህራኑ ከመጽሐፉ ዝግጅት በፊትም ሆነ በኋላ አስተያየት የመስጠት ዕድል ማግኘት አለማግኘታቸውን ለማወቅ ለቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

ጥያቄ 8 ከመጽሐፉ ዝግጅት በፊትም ሆነ በኋላ አስተያየት የመስጠት ዕድል አግኝተው ያውቃሉ?

| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥ | በመቶኛ |
| ሀ | አግኝቻለሁ | 7 | 15.2 |
| ለ | አላገኘሁም | 39 | 84.8 |
| | ድምር | 46 | 100 |

በመጽሐፉ ዝግጅት ላይ አስተያየት በመስጠት ረገድ 7(15.2%) መላሾች እንደተሳተፉ ሲያመለክቱ 39(84.8%) መላሾች ግን እንዳልተሳተፉ ጠቁመዋል። ይህም አብዛኞዎቹን መላሾች ያላሳተፈ በመሆኑ መምህራኑ በማስተማር ተግባር ላይ እያሉ ያስተዋሏቸው ነጥቦች መጽሐፉን ለማሻሻል ሊረዱ የሚችሉ አስተያየቶች ለመሆናቸው ግንዛቤ አለመወሰዱን ለመገመት ተችሏል።

የስምንተኛ ክፍል የጽህፈት ክሂል ይዘት አደረጃጀትን በተመለከተ የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ይዘቶቹ ከዓላማው ጋር ያላቸው መጣጣም ላይ ችግር እንዳለባቸው ሲሆን የይዘት መምረጫ መስፈርቶችም በአግባቡ ስራ ላይ ውለው አልታዩም ። ተከታታይነትና ውህደትን የሚያሳዩ ይዘቶች ያሉባቸው ሲሆኑ

በተለጣጣቂነት በኩል ግን የአብዛኛዎቹ ይዘቶች አቀራረብ የተዛባና ችግር ያለባቸው ሆነው ተገኝተዋል።

በአጠቃላይ የእርከኑን የጽህፈት ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት በተመለከተ ይዘቶቹ ከዓላማ ጋር መጣጣም ማጣታቸውና ተለጣጣቂነታቸው አለመጠበቁ የሁሉም ክፍሎች የጋራ ችግሮች ሆነው ተገኝተዋል። በተጨማሪም በዚህ ጥናት አቅራቢ እምነት አብዛኛው የደረጃው መምህራን በመጽሐፍ ዝግጅትና አስተያየት በመስጠት አለመሳተፋቸው ለችግሩ መባባስ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

4.1.3. ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ባሉት መጻህፍት ላይ ያሉትን ይዘቶች ከአደረጃጀት መርሆች አኳያ ብቃታቸውን ለመለየት በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ሰንጠረዥ 28

ይዘቶቹ የተከታታይነትን መስፈርት የጠበቁ መሆን አለመሆናቸውን ለመለየት የተሰበሰቡ መረጃዎች መግለጫ

| የጽህፈት ክሂል ይዘቶች | የክፍል ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|
| ቃላት | 5 | 6 | 7 | 8 |
| ዐረፍተነገር | 5 | 6 | 7 | 8 |
| አንቀፅ | 5 | 6 | 7 | 8 |
| የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ | 5 | 6 | 7 | 8 |
| ስርዓተ ነጥቦች | 5 | 6 | 7 | 8 |
| ግጥም መፃፍ | - | 6 | 7 | 8 |
| ደብዳቤ | 5 | 6 | 7 | - |
| ሪፖርት | - | 6 | 7 | - |
| መረጃ መሰብሰብ ( መተንተን) | 5 | - | - | 8 |
| ማስታወሻ ማስቀረት | - | 6 | 7 | - |
| አስተዋጽኦ መንደፍ | - | 6 | - | - |
| የረቂቅ ምንነትና አዘገጃጀት | - | - | 7 | - |
| ጥናትና ምርምር ማድረግ | - | 6 | 7 | - |
| የእጅ ጽህፈት | - | 6 | 7 | - |
| የሆሄያት ቅርፅ | - | - | 7 | - |

(ለዝርዝሩ አባሪ 'ሐ' ይመለከቷል )

ተከታታይነት አንድን ክሂል ያጎለብታሉ ተብለው የሚታሰቡ ጠቃሚ ነጥቦች ተደጋግመው እንዲቀርቡ የሚደረግበት መስፈርት መሆኑን በምዕራፍ ሁለት ለመግለፅ ተሞክሯል። በዚህም መሠረት እነዚህ ከላይ በቀረቡት በአራቱ ክፍሎች ይዘቶች

አማካይነት የተከታታይነት መርህ በመጠኑ እንደተጠበቀ እናያለን። ስለቃላት ፤ ዓረፍተነገር ፤ አንቀፅ፤ የሕይወት ታሪክና ስርዓተ ነጥቦች የቀረቡት ይዘቶች በአራቱም ክፍል ተደጋግመው ይታያሉ። ይዘቶቹ ለጽህፈት ክሂል መዳበር ያላቸው ጠቀሜታ የታሰበበት መስሎ ይታያል። በሌላ በኩል ደግሞ ሪፖርት ፤ ጥናትና ምርምር ለስድስተኛ ሰባተኛ ክፍሎች ቀርቦ በስምንተኛ ክፍል አይታይም አስተዋጽኦ መንደፍም በስድስተኛ ክፍል ብቻ ሲታይ የረቂቅ አዘገጃጀት ደግሞ በሰባተኛ ክፍል ብቻ ቀርቧል። የእጅ ጽህፈት በአምስተኛ ክፍል ሳይቀርብ ስድስተኛ ሰባተኛ ክፍል እንዲቀርብ ተደርጓል።

ከነዚህ ይዘቶች ለመረዳት እንደተቻለው የይዘቶቹ ተከታታይነት የተማሪውን ደረጃ ያላጤኑ መሆናቸውን ነው። አንድ ጊዜ ብቻ የሚቀርብ ይዘት ክሂልን በማዳበር ረገድ ያለውን ጠቀሜታ አነስተኛነት ያለመገንዘብ ችግር እንዳለ ማስተዋል ይችላል። በተጨማሪም የደብዳቤ አፃፃፍ በስምንተኛ ክፍል እንዲቀርብ አልተደረገም። በዚህ የእርከኑ ትምህርት ማጠናቀቂያ በሆነው ክፍል ደብዳቤ አለመካተቱ የተከታታይነት አደረጃጀት ችግር መኖሩን ያሳያል።

ሰንጠረዥ 29

ይዘቶቹ የተለጣጣቂነትን መስፈርት የጠበቁ መሆን አለመሆናቸውን ለመለየት የተሰበሰቡ መረጃዎች መግለጫ

ሀ.

| የጽህፈት ክሂል ይዘቶች | የክፍል ደረጃ |
|---|---|
| ቃልን አገጣጥሞ ዐረፍተነገር መመስረት | 5 |
| አንቀፅን ማደራጀት | 6 |
| አንቀፅን ማሳጠር | 7 |
| የፈጠራ ፅሁፍ መፃፍ | 8 |

እነዚህ ይዘቶች ወደ ፈጠራ ፅሁፍ ለመድረስ ከሞላ ጎደል ከቀላል ወደ ከባድ የተደራጁ ናቸው። የተማሪዎቹን ደረጃ የመመጠናቸው ጉዳይ ግን ጥያቄ ላይ የሚወድቅ ነው።

ለ.

| የጽህፈት ክሂል ይዘቶች | የክፍል ደረጃ |
|---|---|
| አንቀፆችን ከአንድ ዓረፍተነገር ማሳጠር | 6 |
| አንቀፅን ከ 5- 6 በሚደርሱ ዓነገሮች ማሳጠር | 7 |

በነዚህ ይዘቶች መረጃነት ደግሞ ሌላ ሁኔታን መረዳት ይቻላል።

የዝቅተኛው ክፍል ተማሪ አንቀፆቹን ጨምቆ በአንዲት ዓረፍተነገር የማሳጠር ልምድ እንዲያዳብር ሲጠበቅበት የከፍተኛው ክፍል ተማሪ ግን አንቀጾቹን ከአምስት እስከ ስድስት በሚደርሱ ዐርፍተ ነገሮች እንዲያሳጥር ይደረጋል። በዚህ ጥናት አቅራቢ እምነት ይዘቶቹ ከቀላል ወደ ከባድ የተደራጁ ሆነው አልተገኙም። የትኛው ከባድ እንደሆነ በማጤን በተማሪው ደረጃ የማስቀመጥ ችግር እንዳለ የሚጠቁም መረጃ ሆኖ ታይቷል።

ለ

| የጽህፈት ክሂል ይዘቶች | የክፍል ደረጃ |
| --- | --- |
| የደብዳቤ ቅርፅ | 5 |
| ከስራ ቢቀሩ ምክንያትን በጽሁፍ መግለፅ | 6 |
| የብዕር ጓደኛ ደብዳቤ | 6 |
| የቤተሰብ ደብዳቤ | 7 |
| ........................ | 8 |

ከመረጃው በመረዳት እንደሚቻለው የአምስተኛ ክፍል ተማሪ የደብዳቤን ቅርፅ ይለማመዳል። ይህም በተማሪው ደረጃ የሚመጥን ሆኖ ተገኝቷል። የስድስተኛ ክፍል ተማሪ የሚፅፉትው የስራና የብዕር ጓደኛ ደብዳቤዎችን ሲሆን የሰባተኛው ክፍል ተማሪ ደግሞ የቤተሰብ ደብዳቤ ይለማመዳል። የትምህርት ይዘቶችን ከቅርብ ወደ ሩቅ ማደራጀት አንዱ የተለጣጣቂነት ገፅታ እንደሆነ ባለፈው ምዕራፍ ተገልጿል በዚህም መሠረት የቤተሰብ ደብዳቤ ለዝቅተኛው ክፍል፤ የስራ ደብዳቤ ለከፍተኛው ክፍል አለመቅረቡ የአደረጃጀት ችግር እንዳለ ያሳያል። በስምንተኛ ክፍል ደብዳቤ አለመወሳቱም ከዚሁ ጋር የሚታይ ይሆናል ።

መ.

| የጽህፈት ክሂል ይዘቶች | የክፍል ደረጃ |
| --- | --- |
| ........................ | 5 |
| የእጅ ፅህፈት | 6 |
| የእጅ ጽሕፈት ማሻሻል | 7 |
| የእያንዳንዱን ሆሄ ቅርፅ በትክክል መፃፍ | 7 |

